Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

Department of PreK–12 Curriculum and Districtwide Programs
Office of Curriculum and instructional Programs
ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል የሥርአተ ትምህርት እና ዲስትሪክት አቀፍ ፕሮግራሞች
የስርአተ ትምህርት እና የማስተማር ፕሮግራሞች ቢሮ



# የመዋእለ ህፃናት ትምህርት መመሪያ መፅሔት (Handbook)

# 2025–2026









የልጁ(ጷ) ስም

## ራእይ

ለእያንዳንዱ እና ለሁሉም ተማሪ የላቀ ህዝባዊ ትምህርት በመስጠት ትምህርትን እናበረታታለን።

## ተልእኮ

እያንዳንዱ(ዷ) ተማሪ በኮሌጅ እና በሥራ መስክ ውጤታማ እንዲሆን/እንድትሆን፣ በአካደሚክስ፣ ችግር የመፍታት ዘዴ/ብልሃት ፈጠራ፣ እና የማህበራዊ ስሜት ክህሎቶች ይኖሩታል/ይኖሯታል።

## ዋና ዓላማ

ሁሉም ተማሪዎች የወደፊት ህይወታቸው የበለፀገ እንዲሆን ማዘጋጀት።

## ዋና ዋና እሴቶቻችን

ትምህርት መስጠት/እውቀት ማስጨበጥ፣
ግንኙነት ማዳበር፣
አክብሮት፣
ልቀት፣
ፍትኃዊነት።


**የትምህርት ቦርድ**
**Board of Education**

**ሚ/ስ ጁሊ ያንግ**
Ms. Julie Yang
**ፕሬዚደንት**
President

**ሚ/ስ ግሬስ ሪቬራ-ኦቨን**
Ms. Grace Rivera-Oven
**ም/ፕሬዚደንት**
Vice President

**ሚ/ስ ሪታ ሞንቶያ**
Ms. Rita Montoya

**ሚ/ስ ካርላ ሲልቨስትሪ**
Ms. Karla Silvestre

**ሚ/ስ ላወራ ስቲዋርት**
Mrs. Laura Stewart

**ሚ/ስ ብረንዳ ዎልፍ**
Ms. Brenda Wolff

**ሚ/ስ ናታሊ ዚመርማን**
Ms. Natalie Zimmerman

**ሚ/ር ፕራኒል ሱቫርና**
Mr. Praneel Suvarna
**ተማሪ አባል**
Student Member

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
Montgomery County Public Schools

**ቶማስ W. ቴይለር (ዶ/ር)**
Thomas W. Taylor, Ed.D., M.B.A.
**የት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት**
Superintendent of Schools



15 West Gude Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

# ወደ መዋእለ ህፃናት እንኳን ደህና መጣህ(ሽ)

Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

**OFFICE OF THE SUPERINTENDENT OF SCHOOLS**

ፌብሩዋሪ 2025

ውድ ወላጅ/አሳዳጊ
እንኳን ደስ አለዎት! ፎል/በልግ ላይ ልጅዎ ወደ መዋእለ ህጻናት/ኪንደርጋርተን ለመግባት ሲዘጋጅ (ስትዘጋጅ) እርስዎ እና ቤተሰብዎ በጣም አስፈላጊ የሆነ እርከን ደረሳችሁ ማለት ነው። የልጅዎን የትምህርት ቤት ተሞክሮ ደስተኛ እና ስኬታማ ለማድረግ ከእርስዎ ጋር ለመስራት በጉጉት እንጠባበቃለን። ለ 21ኛው ክፍለ ዘመን ስኬታማ እና አምራች ዜጎችን ለማዘጋጀት ትናንሽ ልጆች የሆኑ ተማሪዎቻችን ከጅምሩ የዳበረ ሁለገብ ትምህርት ማግኘት እን ዳለባቸው እናምናለን። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመዋዕለ ሕፃናት ፕሮግራም ከሀገር ውስጥ ምርጥ ከሚባሉት መካከል በስፋት ይታወቃል፣ ተማሪዎች በትምህርት ዲስትሪክቱ የማንበብ እና የሂሳብ ግቦች ላይ ጥሩ እድገት እያሳዩ ናቸው።

በሜሪላንድ ህግ መሠረት ሴፕቴምበር 1, 2025 ዕድሜው(ዋ) 5 ዓመት የሆነ(ች) ልጅ፣ ትምህርት ቤት መግባት አለ በ(ባ)ት። ይህ የመዋዕለ ሕፃናት መመሪያ መጽሔት ስለ MCPS የመዋዕለ ሕፃናት መርሃ ግብር መረጃ ይሰጥዎታል። ልጅዎን ለመዋዕለ ሕፃናት ለማስመዝገብ ለአካባቢዎ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማቅረብ የሚያስፈልጉዎትን ሁሉንም ቅጾች ያካትታል። ልጅዎን ወደ ት/ቤታችን ሲስተም ለመቀበል በጉጉት እንጠብቃለን። በሚያስመዘግቡበት ጊዜ፥ እባክዎ የሚከተሉትን መረጃዎች ወይም ሠነዶች ያምጡ፦

- የልጅዎ የልደት ሠርተፊኬት ወይም ሌላ የእድሜ ማረጋገጫ (ፓስፖርት ወይም የሐኪም የምስክር ወረቀት) ያስ ፈልጋል።
- ፍቃድ ባለው የልጅዎ የጤና ባለሙያ የተሞላ የሜሪላንድ የክትባት ምስክር ወረቀት አስፈላጊ ነው። የክትባት ማስረጃው ወቅታዊ እንዲሆን ካስፈለገ የት/ቤቱ የማህበረሰብ ጤና ነርስ ያሳዉቅዎታል/ታሳዉቅዎታለች።
- ልጅዎ ከዘጠኝ ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወይም በተመዘገበ(ች)በት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የአካል ምርመራ ያደረገ(ች)በት ማረጋገጫ። (የጤና ምርመራ መደረጉን የሚያረጋግጥ ሰነድ ከዚህ ቀደም አስገብተው ፋይል ዉስጥ ካለ፣ ሌላ ማቅረብ አያስፈልግም)
- ልጅዎ ባለፈው አመት መዋእለ ህፃናት ከመከታታል ነፃ ተብሎ/ላ ከነበረ የተሞላ MCPS ቅጽ 560-19፣ (Exemption to Kindergarten Attendance Requirement) ።
- በሞንትጎመሪ ካውንቲ የነዋሪነት ማረጋገጫ።
- የእርስዎን ህጋዊ መታወቂያ እና ልጅዎ መሆኑ(ኗ)ን የሚያረጋግጡበት ማስረጃ።
- በዚህ የመዋእለ ህፃናት ትምህርት መመሪያ መጽሔት ላይ ያሉትን ቅጾች ሞልተው ያቀርባሉ።
- ለልጅዎ ደህንነት ይጠቅማሉ የሚሏቸውን ማናቸውም መረጃዎች (ለምሳሌ፡- ለልጅዎ አለርጂ የሚሆኑ ነገሮች፥ የሚወሰዱ መድሃኒቶች፣ ወይም የአመጋገብ መረጃ)።

እባክዎ ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ወደ ልጅዎ የአካባቢ ት/ቤት ያቅርቡ። ልጅዎ በመዋለ ህፃናት ቆይታው(ዋ) አመት ከልጅዎ ትምህርት ቤት ጋር ጠንካራ የአጋርነት ድጋፍ ለመገንባት ከሚወስዱት ከብዙ እርምጃዎች የመጀመሪያው እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን።

ከልብ

Thomas W. Taylor, Ed. D, M.B.A.
Superintendent of Schools

የት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት

# ማውጫ

ስለ መዋእለ ህፃናት . . . . . 1
የመዋእለ ህፃናት ግቦች . . . . . 1
ለት/ቤት መዘጋጀት . . . . . 1
ት/ቤት መከታተል አስፈላጊ ነው . . . . . 1
የመዋእለ ህፃናት ፕሮግራም . . . . . 1
ልዩ ትምህርት/ስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎት የሚያገኙ ልጆች . . . . . 2
የመጀመሪያ ቋንቋቸው እንግሊዘኛ ያልሆነ እና በእንግሊዝኛ እና በሌሎች ቋንቋዎች ችሎታቸውን በማዳበር ሂደት ላይ ያሉ ተማሪዎች፥ Emergent Multilingual Learners . . . . . 2
ስለ ልጅዎ የማሻሻል ሒደት . . . . . 2
የወላጅ-የመምህር ስብሰባዎች . . . . . 2
ስለ ልጅዎ ት/ቤት ጉብኝት . . . . . 2
ወላጆችም/አሳዳጊዎችም አስተማሪዎች ናቸው . . . . . 2
መዋእለ ህፃናት ከሚማር/ከምትማር ልጅዎ ጋር በቤት የሚሰሩ ስራዎች . . . . . 3
ወደ መዋእለ ህፃናት መግባት . . . . . 3
ልጅዎ መዋእለ ህፃናት እየጀመረ(ች) ነው . . . . . 3
የእርስዎን መዋእለ ህጻናት ት/ቤት ያግኙ . . . . . 4
ተፈላጊ ሠነዶች . . . . . 4
የልጅዎን ጤንነት መጠበቅ . . . . . 5
ልጅዎን ከት/ቤት አስቀርተው ቤት ስለማቆየት . . . . . 5
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት ለምዝገባ የጤና ጥበቃ መስፈርቶች-የትምህርት ቤት ጤና አገልግሎት . . . . . 6
የጥንቃቄ/የደህንነት መረጃ . . . . . 7
በቤትና በት/ቤት መካከል መደረግ ስላለበት የደህንነት ጥንቃቄ፡- በት/ቤት አውቶቡስ መጓዝ . . 7
ወደ ት/ቤት በእግር መሄድ . . . . . 8
አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የቋንቋ ኢመርዥን ፕሮግራም . . . . . 8
ትምህርት የሚሰጠው በየትኞቹ ቋንቋዎች ነው? . . . . . 8
ልጄ እንዴት ሊሳተፍ/ልትሳተፍ ይችላል/ትችላለች? . . . . . 8
የወላጅ (ፓረንት) አካደሚ . . . . . 9
የልጅ እንክብካቤ ስለመምረጥ . . . . . 9
ስለ ት/ቤቶች መዘጋት . . . . . 9
ቅጾች እና ምዝገባ . . . . . 10
የግንኙነት መረጃ . . . . . 30
የቅድመ መዋዕለ ህፃናት/ሄድስታርት ተማሪ ምዝገባ መረጃ . . . . . 31

# መዋእለ ህፃናት

- ልጅዎ ሊያድግና ሊማር የሚችልበት/ልታድግና ልትማር የምትችልበት አስተማማኝ ቦታ ነው፣
- እርስዎ እና የልጅዎ አስተማሪ የጋራ ድጋፍ መስጠት የምትች ሉበት ቦታ፣
- የማስተማር ፕሮግራሙ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ከሚገኙ ልጆች ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣምበት ቦታ ነው፣
- ልጅዎ በማንበብ፣ በመፃፍ፣ በሂሳብ፣ በትላልቅ- እና በትናንሽ-የቡድን ትምህርቶች፣ እና የትምህርት ማእከሎችን በመሳሰሉ የተለያዩ የትምህርት ተሞክሮዎች የሚሳተፍበት/ የምትሳተፍበት ስፍራ ነው፣
- የልጅዎን የማወቅና የአዲስ ግኝት ጉጉትና ደስታ የሚያበ ረታታ ቦታ ነው፣
- ልጅዎ ልዩና ብርቅ ሆና/ኖ ተቀባይነት የሚያገኝበት/የምታገ ኝበት ስፍራ ነው፤ እናም
- ራስን ማክበርና በራስ መተማመንን የሚጠናከርበት ቦታ ነው።

## የመዋእለ ህፃናት ግቦች

በራስ መተማመንን ማሳደግ በ —

- መከበርና ዋጋ ማግኘት፤
- ስኬትን መለማመድ፤ እና ስሜትን በተገቢ ሁኔታ መግለፅ።

የመማር ዘይቤዎች—

- መመርመር እና አማራጭ መውሰድ፣ በግል፣ በጥንድ፣ ከብዙ እና ጥቂት ቡድኖች ጋር መስራትና መጫወት፣
- ሃሳብን እና አስተያየትን መግለፅ፤ እና
- ችግሮችን በአግባቡ መፍታት።

እውቀትንና ክህሎትን በሚከተለው አኳኋን ማዳበር—

- ማዳመጥ፣ ማንበብ፣ ንግግር፣ እና መፃፍ፣
- ዕቃዎችን መሰብሰብ፣ በትኩረት ማጤን፣ በስም መለየት፣ እና በአይነት እየለዩ መደርደር፣
- መቁጠርና ማነፃፀር፣ ማወዳደር እና
- ከመፃህፍትና ከተሞክሮዎች ታሪኮችንና ሃሳቦችን ማጋራት።

## ለት/ቤት መዘጋጀት

ት/ቤት የደስታና፣ የወዳጅነት ቦታ መሆኑን በመንገር ልጅዎን ለዚህ አዲስ ተሞክሮ እንዲዘጋጅ-እንድትዘጋጅ ማገዝ ይችላሉ። ጥያቄዎችን በቅንነት ለመመለስ ይሞክሩ- የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ በዚህ መምሪያ መጽሐፍ (handbook) ላይ የሚገኘውን መረጃ ይጠቀሙ ወይም ወደ ት/ቤት ይደውሉ።

ስለ ት/ቤት እርስዎ የሚኖርዎት አመለካከት ለልጅዎ ስኬት በጣም ጠቃሚ ነው። ከአሁኑ አወንታዊ ነገሮችን ከእርስዎ መስማት ጥሩ ልማዶችን ማዳበር ያስችላል። ስለ ት/ቤት የሚያሳስብዎት ነገር ካለ ከልጅዎ ጋር ሳይሆን ከአስተማሪ ወይም ከርእሰመ ምህር ጋር ይነጋገሩ። ልጅዎ ከሌሎች ልጆች ጋር እንዲጫወት-እንድትጫወት፥ መጫወቻዎችና የመጫወቻ ቦታ እንዲጋራ/እንድ ትጋራ እድል ይስጡ። በተለይ የእርስዎ ልጅ ቀደም ያለ የት/ቤት ልምድ ከሌለው/ከሌላት ይሄ ከትምህርት ቤት ጋር ለመለማመድ ቀላል ያደርገዋል።

ልብሶችንና መጫሚያዎችን፣ አሻንጉሊቶችን፣ መጫወቻዎችን እና የመፀዳጃ ፍላጎቶችን ልጅዎ ራሱን-ራሷን በመቻል አጠቃቀሙን እንዲያውቅ/እንድታውቅ ያደፋፍሩ። ልጅዎ ልብሶቹ(ቿ)ን መቆለፍ፣ በቅልጥፍና መፍታት እንዲለማመድ/እንድትለማመድ፣ እና የልብሶ ቹ(ቿ)ን ዚፕ መቆለፍ እና የጫማ ክሮችን ማሰር እንዲለማመድ/ እንድትለማመድ ያድርጉ። ልብሶች በቀላል ሊቆለፉ የሚችሉና ዚፕ የሚደረጉ መሆናቸውን ወይም Velcro® እና በቀላሉ የሚታጠቡ መሆናቸውን ያስረዱ። ጫማዎች ምቹና በልጅዎ ልክ መሆን አለባቸው። ቦት ጫማ፣ ቆብ፣ የብርድ ጃኬት፣ እና ጓንቶች ለብርዳማ ቀኖች አስፈላጊ ናቸው።

ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን ጀምሮ መደበኛ ስራዎችን መወሰን አስፈላጊ ነው። ልጅዎ በአውቶቡስ የሚጓዝ/የምትጓዝ ከሆነ፣ በእግር ወይም በመኪና ወደ ትምህርት ቤት የሚሄድ/የምትሄድ ከሆነ፤ ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን ጀምሮ መደበኛ የመጓጓዣ ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ነው። ወደ ትምህርት ቤት ከመጡ፣ እባክዎ ለልጅዎ ወደ ህንፃው የመግባት ሂደቶችን፣ ለብቻው(ዋ) ወደ ክፍል መሔድ፣ እና ሰልፍን ጨምሮ መደበኛውን የትምህርት ቤት አሠራር እንዲከተል/እንድትከተል በትክክል መንገርዎን ያረጋግጡ።

## ዘወትር ትምህርት ቤት መገኘት አስፈላጊ ነው

በህመም ወይም በሌላ ድንገተኛ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር፣ በየጊዜው ት/ቤት መገኘት እና በጊዜ መድረስ የእርስዎ ልጅ ስለ ት/ቤት በሚያዳብረው/በምታዳብረው አመለካከት ላይ ጉልህ ሚና ይኖረዋል። በየቀኑ ወደ ት/ቤት መሄድ ወላጅ/አሳዳጊ ወደ ስራ ከመሄድ ጋር ሊነፃጸር ይችላል። የሃላፊነት ስሜትና አዘውትሮ የማከ ናወን ልማድ ልጅዎ ምቾትና ደህንነት እንዲሰማው/ት ያግዛል። ስለ ትምህርት ቤት እና በመደበኛነት ት/ቤት የመከታተል አዎንታዊ አመለካከት በጠቅላላ የትምህርት ዘመናቸውን ሁሉ በየቀኑ ት/ቤት የመከታተል ልማድ ሆኖ ይቀጥላል።

ት/ቤት ማለት የዕለት-ተዕለት ሁነት መሆኑን በልጅዎ አእምሮ እንዲ ሠርፅ በተለይ በመዋዕለ ህፃናት በየቀኑ በት/ቤት ማሳለፍ በጣም አስፈላጊ ነው። ይልቁንም፥ ማህበራዊ እድሎችን እና መዋዕለ ህፃናት በእጃቸው እየሠሩ የመማር አይነት ተሞክሮዎችን ማገጣጠም አስቸጋሪ ነው።

## የመዋእለ ህፃናት ፕሮግራም

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መዋእለ ህፃናት ፕሮግራም መሰረት ያደረገዉ የተማሪዎችን የማንበብ፣ የመጻፍ እና የሂሳብ ችሎታን በሚያጎለብት ሥርአተ ትምህርት ላይ ነው። ለሁሉም ተማሪዎች ሳይንስ፣ ማህበራዊ ጥናት (ሶሻል ስተዲስ)፣ እና ስነጥበብን-ማዋሃድ ላይ አጽንኦት ይሰጣል— እንዲሁም አዳጋች የትምህርት ተሞክሮዎችን ያቀርባል።

ልጆች በትላልቅ- እና በአነስተኛ-ቡድን መማር እና በአስተማሪዎች የሚመሩ ተሞክሮዎችን በሚያካትቱ የተለያዩ የመማር ክንውኖች ላይ ይሳተፋሉ። በመዋእለ ህፃናት ቀን፣ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለመጠቀም፣ ከሌሎች ልጆች ጋር ለመነጋገርና ለመጫወት፣ በጨዋታ ማእከ ሎችና በፕሮጀክቶች የተማሩትን ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ እድሎች ይኖራቸዋል። የመዋእለ ህፃናት አስተማሪ እያንዳንዱ ልጅ ያገኘ(ች) ውን እውቀትና ክሂሎቶች ለመሰነድ እንዲቻል እያንዳንዱን ለውጥና ማሻሻል በጥንቃቄ እየተከታተለ(ች) ይመዘግባል/ትመዘግባለች። በተጨማሪ፣ የተማሪዎችን ፕሮብሌም የመፍታት ችሎታ ለማዳበር፣ አስተማሪዎች ብዙ ቀልጣፋ፣ በተግባር እያከናወኑ የመማር ልምም ዶችን ይሰጧቸዋል።

## ልዩ ትምህርት/ስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎት የሚያገኙ ልጆች

የልዩ ትምህርት አገልግሎት የሚያገኙ ተማሪዎች የአካል ጉዳተኛ ካልሆኑ እኩዮቻቸው ጋር ተመሳሳይ የሆነ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥርዓተ ትምህርት በመጠቀም ይማራሉ። በልዩ ሁኔታ የተነደፈ/ዲዛይን የተደረገ ማስተማር እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ንግግር/ቋንቋ፣ የአካል እና ኦኩፔሽናል ቴራፒ የመሳሰሉ የተለዩ የአካል ጉዳተኛ ልጆች በግለሰባዊ የትምህርት መርሃ ግብራቸው (IEP) መሠረት ይሰጣቸዋል። በመመዘኛው ላይ በተገለፀው መጠን የልዩ ትምህርት አገልግሎት የሚያገኙ ተማሪዎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ ከእኩዮቻቸው ጋር ይማራሉ። ተማሪዎች የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን የሚያገኙት ከአጠቃላይ የትምህርት ሁኔታ ውጭ IEP ቡድን (ወላጆች/አሳዳጊዎችን ጨምሮ) በአጠቃላይ የትምህርት ክፍሎች ውስጥ ተጨማሪ እርዳታዎችን እና አገልግሎቶችን በመጠቀም ለተማሪ ተገቢውን ትምህርት እንደማይሰጥ ሲወስን ነው።

በአሁኑ ጊዜ MCPS ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ልዩ ትምህርት ፕሮግራም የተመዘገበ(ች) ልጅ ካለዎት፣ ለመዋዕለ ሕፃናት ተገቢውን የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ለመወያየት እና ለመወሰን IEP ስብሰባ ይካሄዳል።

## የመጀመሪያ ቋንቋቸው እንግሊዘኛ ያልሆነ እና በእንግሊዝኛ እና በሌሎች ቋንቋዎች ችሎታቸውን በማዳበር ሂደት ላይ ያሉ ተማሪዎች፥Emergent Multilingual Learners

በፌዴራል እና በስቴት መስፈርቶች መሠረት፣ ለመጪዎቹ የመዋዕለ ሕፃናት ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች በሙሉ ስለቋንቋው መረጃ ለመስጠት MCPS ቅጽ 560-24፣ አዲስ የተማሪ መረጃ (ገጽ 11) የሜሪላንድ ቤት ውስጥ ስለሚነገሩ ቋንቋዎች ጥናት፥ ልጃቸው በቤት ውስጥ ስለሚናገረው/ስለምትናገረው ቋንቋ ቅጽ (ገጽ 11) መሙላት አለባቸው። በስቴት ህግ መሠረት፥ ትምህርት ቤቶች በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ ለተጨማሪ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት (ELD) ፕሮግራም ተማሪዎችን ለመለየት ይህንን መረጃ ይጠቀማሉ። ነገር ግን መረጃው ስለ ኢሚግሬሽን በሚመለከት ጉዳይ ጥቅም ላይ አይውልም ወይም ለኢሚግሬሽን ባለስልጣናት ሪፖርት አይደረግም። በምልመላው ውጤት መሰረት ተማሪዎች የመዋዕለ ሕፃናት ትምህርት ፕሮግራም አካል ተደርጎ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማዳበር (ELD) አገልግሎቶች ሊሰጣቸው ይችላል።

## የእርስዎ ልጅ ያሳየ(ች)ው መሻሻል

የትምህርት ዓመት በሚጀመርበት ወቅት፣ ከወላጅ/ሞግዚት ጋር የሚደረጉ ስብሰባዎች ልጅዎ በየጊዜው ስለሚያሳያቸው/ስለምታሳያቸው መሻሻሎች/ለውጦች ለእርስዎ እንዴት እንደሚገለጽ እና ሌሎች በርካታ ዝርዝር ሁኔታዎችን ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር ለርእሰመምህር እና ለመምህር ጊዜ ይሰጣቸዋል። ከመምህሩ ጋር የግል ስብሰባዎች ባብዛኛው የሚደረጉት አመቱ አጋማሽ ላይ ነው። አሳሳቢ ጉዳይ ካለዎት በማንኛውም ጊዜ የልጅዎን መምህር በማግኘት ስለልጅዎ የሚያሳስብዎትን ጉዳይ ለመወያየት ቀጠሮ መያዝ ይችላሉ። እንዲሁም ስለ ትምህርት ቤት ጉዳዮች ለወያየት ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ለመገናኘት ተዘጋጅቶ(ታ) ከሚጠብቅ የትምህርት ቤቱ ካውንስለር ጋር መነጋገር ያስፈልጋል።

ልጅዎ በዓመት አራት ጊዜ ሪፖርት ካርድ ያገኛል/ታገኛለች። በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ወቅት መጨረሻ ላይ ሪፖርት ካርዶች ወደ ቤት ይላካሉ። በሪፖርት ካርዶቹ ላይ የሚካተተው ስለ ልጅዎ ትምህርት እና ስለ መማር ችሎታዎቹ(ቿ) ተጨማሪ መረጃ ነው።

## የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንስ

ከክፍል አስተማሪ ጋር የሚደረጉ ስብሰባዎች ስለ ልጅዎ መረጃ ለመጋራት በጣም ጥሩ እድሎችን ይሰጣሉ። መምህር ልጅዎ በትምህርት ቤት ውስጥ እንዴት/ምን እንደሚሰራ/እንደምትሠራ ሊነግርዎት ይችላል/ልትነግርዎት ትችላለች፤ እርስዎም ልጅዎ በቤት ውስጥ ምን እንደሚያዘወትር/እንደምታዘወትር ለአስተማሪ መግለጽ ይችላሉ። እርስዎ እና አስተማሪው(ዋ) አብራችሁ ልጅዎ እንዴት የበለጠ ለመማር እንደሚችል-እንደምትችል መቃኘት ትችላላችሁ።

የዚህ አይነቱ ቀጣይነት ያለው ግንኙነት በመኖርያ ቤትና በት/ቤት መካከል ዘላቂ ወደሆነ ትብብር ሊያመራ ይችላል። እንደዚህ አይነቶቹ ትብብሮች ከዳበሩ፣ ልጃችሁ ለሚያስደስትና ስኬታማ ለመሆን የበለጠ እድል ይኖረዋል/ይኖራታል።

## የልጅዎን ት/ቤት ስለመጎብኘት

ት/ቤቱንና የልጅዎን መማርያ ክፍል እንድትጎብኙ እናበረታታለን። የጉብኝት ፕሮግራም እንዲያዘጋጁ ለት/ቤቱ ይደውሉ። ህንፃው ዉስጥ እንደገቡ ወደ ትምህርት ቤቱ ጽ/ቤት ብቅ ብለዉ የጎብኝ ባጅ ማግኘት እንዳለብዎት ያስታውሱ።

## ወላጆች/አሳዳጊዎችም መምህራን ናቸው

እስካሁን ድረስ የልጃችሁ ተቀዳሚ አስተማሪ እናንተ ነበራችሁ። አሁን እርስዎን የሚያግዝዎት ሌላ አስተማሪ አለ(ች)፣ ይሁን እንጂ የእርስዎ ሚና በጣም አስፈላጊ መሆኑ ይቀጥላል። ልጆች ት/ቤት ባሉበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ ይማራሉ። በት/ቤት የተማሩትን ትምህርት መኖርያ ቤት ውስጥ በልዩ ልዩ ተግባር ልታጠናክሩት ትችላላችሁ። የልጅዎን ትምህርት ለማገዝ የሚረዱ ነገሮችን እነሆ፡-

- ጥሩ አድማጭ ይሁኑ። ልጅዎ እንዲናገር-እንድትናገር ያድርጉ/ይፍቀዱ። "ለምን እንደዚህ ታስባለህ/ታስቢያለሽ? ወይም "ያ" ወይም "ይሄ" ምን ይመስልሃል/ምን ይመስልሻል? ይህንን የሚመስሉ ጥያቄዎችን በማቅረብ ልጅዎን እንዲያስብ-እንድታስብ ያበረታቱ።
- ለልጅዎ በየቀኑ ያንብቡ። ለልጅዎ የሚያስደስቱ መጻሕፍትን ለመምረጥ የትምህርት ቤት እና የህዝብ ቤተመጻህፍት ሠራተኞች ለመርዳት ይችላሉ።
- ልጅዎ ወደ መኖርያ ቤት የሚያመጣውን/የምታመጣውን የት/ቤት ስራ ተመልክተው ሃሳብ ይስጡበት። ላለማየት ችላ ካሉ ወይም ከወረወሩት፣ ልጅዎ በት/ቤት የሚሰራው-የምትሠራው ስራ አስፈላጊ አይደለም ብሎ(ላ) ሊያስብ ይችላል/ ልታስብ ትችላለች።
- ተገቢ የሆኑ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ከልጅዎ ጋር ሆናችሁ ተመልከቱ እና ስለተመለከታችሁት ነገር ተነጋገሩ።
- በት/ቤት ስላሳየው-ስላሳየችው ማሻሻል መደሰታችሁን ልጃችሁ እንዲያውቅ/እንድታውቅ ያረጋግጡ። ልጆች የሚማሩት በተለያዩ የችሎታ ደረጃ ስለሆነ ከክፍል እኩዮቻቸው ወይም ከወንድም/ከእህት ጋር መመዛዘን የለባቸውም።
- ለልጃችሁ የመፃህፍትና ወረቀቶች ማስቀመጫ ልዩ ቦታ ያዘጋጁ። ይህም መሳቢያ (drawer)፣ መደርደርያ፣ ሳጥን፣ ወይም የት/ቤት ስራ ሊጠራቀምበት የሚችልበት ማንኛውም ቦታ ሊሆን ይችላል።

## በመዋእለ ህፃናት ከሚማር-ከምትማር ልጅዎ ጋር ቤታችሁ ውስጥ የሚከናወኑ ነገሮች

ሁሉም ፍላጎቶቻቸው የተሟሉበት በጣም ምቹ የመማርያ አካባቢ ለመፍጠር፣ ልጆች በአእምሯዊ እድገት መስኮች የሚመደቡ ሰባት የተለያዩ ሰፋፊ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ አለባቸው። ልጃችሁን ለትምህርት ስኬታማነት ለማዘጋጀት፣ እነዚህን አብዛኛዎቹን እንቅስቃሴዎች ከልጃችሁ ጋር እቤት ውስጥ መፈጸም ትችላላችሁ።

1. አካላዊ ደህንነትና የእንቅስቃሴ እድገት
   ጤና፣ ንቃት፣ እና የአእምሮ ችሎታ የሚከተሉትን በስኬት ለማከናወን ይረዳል—
   - በመጫወቻ ቦታ ሽቅብ በሚወጣበት መጫወቻ ላይ ወደ ላይ ለመውጣት፣
   - በመጫወቻ መጫወት፣
   - ዝላይ፣ ሩጫ፣ ገመድ ዝላይ፣ እና ግልቢያ፦
   - ብሎኮችን መገንባት፣
   - ልብስ መቆለፍ፣ ዚፕ ማድረግ፣ እና ማሰር፣
   - መፃፍ፣ መሳል፣ ቀለም መቀባት፤ እና
   - ፐዝል ቁርጥራጮችን (puzzles) መገጣጠም።

2. ግላዊና ማህበራዊ እድገት
   ከጓደኞቹ(ቿ)ና ከአዋቂዎች ጋር አወንታዊ ግንኙነት የማድረግ ችሎታ በሚከተለው ሁኔታ ማሳየት—
   - ተራ የመጠበቅ ልምድ መቅሰም፣
   - በቤት ውስጥ ስራዎችን ማገዝ፣
   - ስሜትን መግለፅ፣
   - አሻንጉሊቶችንና የግል እቃዎችን ለቅሞ ማንሳት፣
   - ከሌሎች ልጆች ጋር መጫወት እና
   - ችግር (ፕሮብሌም) ስለመፍታት መማር።

3. ንባብ እና የቋንቋ ስነ ጥበብ እድገት
   በመስማት፣ በመናገር፣ በማንበብ፣ እና በመፃፍ እንደሚከተለው መገናኘትና ሕትመትን መገንዘብ—
   - የፊደላትን ሆሂያት መቁጠር/ማንበብ፣
   - የተጻፈ ስምን ለይቶ ማወቅ፣
   - የራስን ስም መፃፍ፣
   - መፅሃፍ ውስጥ ያሉ ስእሎችን መመልከትና መጽሃፉ ስለምን እንደሆነ መገመት፣
   - መጽሐፍት ማንበብ፣
   - የተነበቡ ታሪኮችን እንደገና መናገር፣
   - የህዝብ ቤተመጻሕፍት መጎብኘት፣
   - በቴፕ ላይ የተቀረጹ ታሪኮችን ማዳመጥ፣
   - ታሪኮችን/ተረቶችን መናገር፣
   - የሕጻናት ግጥሞች እና ዜማዎችን ማነብነብ፣
   - ስለ እለታዊ ክውነቶች፣ ጉዞዎች፣ ሽርሽሮች ማውራት፣
   - በማግኔታዊ የፊደል ሆሄያት መጠቀም እና
   - አዳዲስ ቃላትን መማር።

4. የሂሳብ ስሌት
   ከእለታዊ ቁሳቁሶች ጋር በማገናኘት ስለቁጥሮች ግንኙነት ግንዛቤ እንዳለው/ላት እንደሚከተለው ማሳየት—
   - ቀላል ቅርፀቶችን መለየትና ማስፋፋት፣
   - እለታዊ ሁነቶች ስለሚከወኑበት ወቅት መናገር፣
   - ቁሳቁሶችን በቀለም፣ በቅርፅ፣ ወይም በመጠን ለይቶ መደርደር፣
   - ቁመትን ማወዳደር (የረዘመ፣ ያጠረ)፣
   - እስከ 10 መቁጠር፣
   - አሃዞችን ከ1 እስከ 9 ለይቶ ማወቅ፣
   - በላይ፣ በታች፣ በጎን በመሳሰሉ ቃላት በመጠቀም ቦታን መግለፅ፣
   - ይበልጣል፣ ያንሳል ፣ ወይም ተመጣጣኝ የሆኑ ቁሳቁሶችን እያነፃፀሩ በአይነታቸው መለየት፣ እና
   - ክቦችን፣ ሶስት ማእዘኖችን፣ ካሬዎችን/squares፣ እና አራት ማእዘኖችን መለየትና መግለፅ።

5. ማህበራዊ ጥናቶች
   ስለ ራስ፣ ቤተሰብ፣ ት/ቤት፣ እና ማህበረሰብ እውቀት በሚከተሉት መንገዶች ማጋራት—
   ነገሮች እንዴት እንደሚለወጡ/እንደሚቀያየሩ መወያየት፤
   - በቤተሰብ ስለተከናወኑ ሁነቶች መናገር፣
   - የቤተሰቦችና የጓደኞችን ምስል/ስዕል መስራት፣
   - የጥንቃቄና ደህንነት ደንቦችን መገንዘብ፤ እና
   - በቴክኖሎጂ መጠቀምን መማር።

6. ሳይንሳዊ አስተሳሰብ
   በሚከተለው ዘዴ የማወቅ ችሎታን በመጠቀም አለምን መዳሰስና ትርጉም ማግኘት—
   - በእግር መዘዋወርና አካባቢዎችን መቃኘት፤
   - ስለ አየር ሁኔታዎች፣ አትክልቶች፣ እና እንስሳትን መቃኘት እና መወያየት፤
   - የመለየትና የማወቅ ስሜትን ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ/በጥንቃቄ መጠቀም፤
   - ቁሳዊ ነገርን፣ ክውነትን፣ ወይም እንቅስቃሴን ለመግለፅ ከስሜት አካላት ጋር በተያያዘ የቃላት አጠቃቀም መግለጽ፤ እና
   - የፈለጉትን ነገር ለመመራመር መሳርያዎችንና መገል ገያዎችን መጠቀም (አጉሊ መነፅር፣ ኮምፒውተር፣ መጽሐፍት፣ ፎቶግራፎች፣ ቪድኦች)።

7. ስነ ጥበባት
   በመንቀሳቀስ፣ ሙዚቃ፣ በሚታይ ስነጥበብ፣ እና በትያትር በመያዝ/በመሳተፍ ስሜቶችንና ሃሳቦችን ለመግለፅ የሚከተሉትን ማከናወን፦
   - መዝሙሮችን/ዘፈኖችን መዘመር/መዝፈን፤
   - ሥዕል መሳልና ቀለም መቀባት፣
   - በሙዚቃ መደነስ፣
   - ቅቦችን፣ ስእል መሣያ እርሳሶች፣ ጠመኔ፣ እና ሸክላ ጭቃ ምን እንደሚሠራበት መመራመር፤ እና
   - በዓይነ ህሊና የተቀረጹ የተለያዩ ገፀባህርያትን መጫወት/ትያትር መስራት።

# መዋእለ ህፃናት መግባት

## ልጅዎ መዋእለ ህፃናት እየጀመረ/ች ነው።

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ በሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ በጠቅላላ ቅድመ መዋእለ ህፃናት (Prekindergarten)፣ መዋእለህ ፃናት (Kindergarten)፣ እና 1ኛ ክፍል ለሚገቡ ህፃናት ስለተወለ ዱበት ቀን መመሪያ አውጥቷል። ይኼውም በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሚገኙ ኤሌሜንታሪ ት/ቤቶችን ያጠቃልላል። ወደ መዋእለ ህፃናት ለመግባት ልጆች ሴፕቴምበር 1 ላይ 5 ዓመት እድሜ ሊሆናቸው ይገባል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ("Board Policy JEB" የተሰኘ ወደ ቅድመ መዋእለ ህፃናት፣ መዋእለ ህጻናት፣ እና አንደኛ ክፍል ቀደም ብሎ ስለመግባት ) ከሴፕተምበር 1 ቀን በኋላ የሚወለዱ ልጆችን ወደ መዋእለ ህጻናት ቀደምብሎ የመግቢያ ፖሊሲ አለው። ቀደምብሎ ማስገባት የሚፈልጉ ወላጆች/ሞግዚቶች በአካባቢያቸው የሚገኘውን ትምህርት ቤት ማነጋገር እና "MCPS Form 271-6" ቅጽ መሙላት አለባቸውመዋእለ ህፃናት ቀደምብሎ ለማስገባት የመጠ የቅያ ቅጽ/Application for Early Entrance to Kindergarten።

2025–2026 የትምህርት ዓመት ከማርች 17፣ 2025 ጀምሮ በአካል የምዝገባ ክፍለ ጊዜዎች ይካሄዳሉ።

በሰመር ወቅት ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ በነዋሪነት የሚመጡ ቤተሰቦች በተቻለ ፍጥነት ልጆቻቸውን ማስመዝገብ ይኖርባቸዋል። የትምህርት ቤት ቢሮዎች አመቱን በሙሉ ክፍት ናቸው። በተቻለ ፍጥነት ወደ ት/ቤቱ ደውለው ቀጠሮ እንዲይዙ እናሳስባለን።

## ትምህርት ቤትዎን ስለማግኘት

MCPS የልጅዎን የአካባቢ ት/ቤት የሚወሰንበት ክልል አለው። እርስዎ የሚኖሩበትን አካባቢ የሚያገለግለውን ት/ቤት ክልል መረጃ ለማግኘት ከሰኞ እስከ ዓርብ 9:00 a.m. – 5:00 p.m በስልክ ቁጥር፡- 240-314-4710 ይደውሉ። የትምህርት ቤት የቤት ሥራ መስሪያ መሣሪያ መጠቀም ይችላሉ/School Assignment Tool MCPS ድረገጽ ላይ ይገኛል ወይም እርዳታ ለማግኘት BoundaryInquiries@mcpsmd.org ኢሜል ያድርጉ።

## ተፈላጊ ሠነዶች

ልጆችሁን ት/ቤት ለማስመዝገብ ሰነዶች ያስፈልጋሉ። ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ከእያንዳንዱ አንዳንድ መለያ እንዲኖርዎት ያስፈ ልጋል፡-

### የልጁ(ጅቱ) የእድሜ ማረጋገጫ (የማስረጃዎቹ ምሣሌ ከዚህ በታች ይገኛል)

- የልደት ሠርተፊኬት
- ፓስፖርት/ቪዛ
- የሃኪም ሠርተፊኬት
- የጥምቀት ወይም የቤተክርስቲያን ሠርተፊኬት
- የሆስፒታል ሠርተፊኬት
- የሠነድ ማረጋገጫ ማህተም (ኖቶራይዝ) የተደረገበት የወላጅ ቃለመሃላ ማስረጃ
- ሲወለድ/ስትወለድ የተመዘገበ(ች)በት
- ሌላ ህጋዊ ወይም በህጋዊ ቃል ተቀባይ የተመሰከረ የማንነት ማረጋገጫ

### ተማሪው(ዋ)ን የሚያስመዘግበዉ/የምታስመዘግበዉ ወላጅ(ሞግዚት) የማንነት ማረጋገጫ (ከዚህ በታች በምሣሌነት የተጠቀሱት ሠነዶች ፎተግራፍ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል)

- የመንጃ ፈቃድ
- ፓስፖርት
- ሌላ ህጋዊ መታወቂያ

### ከልጁ/ልጅቱ ጋር የወላጅ(የሞግዚት) ዝምድና/ግንኙነት ማስረጃ(የሠነዶቹ አይነት ምሣሌ)

- የወላጆች ማንነትን የሚገልጽ የተማሪ የልደት ሠርተፊኬት
- የፍርድ ቤት ትእዛዝ
- የመለያየት ስምምነት ወይም የፍቺ ውሳኔ የተሰጠበት
- ሌላ ህጋዊ መታወቂያ

### የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪነት ማስረጃ

- የመኖሪያ ቤት ባለቤት ከሆኑ፣ተቀባይነት የሚኖረው ማስረጃ ወቅታዊ የንብረት ታክስ ማስከፈያ (ቢል) ነው። ቅጂ ከሞን ትጎሞሪ ካውንቲ የፋይናንስ ዲፓርትመንት 240-777-0311 በመደወል ወይም montgomerycountymd.gov/finance ሊገኝ ይችላል፣ ወይም
- ተከራይ ከሆኑ ተቀባይነት የሚኖረው ሠነድ ወቅታዊ የኪራይ ውል/ሊዝ ሲሆን፥ የመጀመሪያው የኪራይ ውል (ሊዝ) ጊዜው ያለፈበት ከሆነ፥ ወቅታዊ የመገልገያዎች ክፍያ መጠየቂያ/ደረሰኝ (utility bill) ወይም ኪራይ የተራዘመበት ማረጋገጫ መቅረብ አለበት። ወይም
- በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ት/ቤት አካባቢ የተረጋገጠ ነዋሪነት ካለዉ/ካላት የቤት ባለቤት ወይም ከተከራይ ጋር በደባልነት የሚኖሩ ከሆነ፣ ማስረጃነቱ የተረ ጋገጠ/ኖቶራይዝ የተደረገ የ MCPS ቅጽ 335-74፣ የደባልነት ማረጋገጫ መሞላት አለበት፣ እናም ተገቢ፣ የነዋሪነት ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው። ለቤት ባለቤቶች፥ ተቀባይነት የሚኖረው ሠነድ ወቅታዊ የባለንብረትነት ታክስ ክፍያ ሠነድ፣ ለተከራይ፣ ተቀባይነት የሚኖረው ሰነድ ወቅታዊ ሊዝ የተፈረመበት ማረጋገጫ (የመጀመሪያው ሊዝ ሠነድ ጊዜው ያለፈበት ከሆነ፥ ወቅታዊ የመገልገያዎች ክፍያ ሠነድ ወይም ኪራይ የተራዘመበት ማረጋገጫ መቅረብ አለበት)፥ የተፈረመበትና የሠነድ ማረጋገጫ ማህተም ያለው "MCPS Form 335-74" ቅጽ፣ እና ወላጅ/ሞግዚት በተጠቀሰው አድራሻ ነዋሪ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ሰነድ ሁለት ቅጂ መቅረብ አለበት። ስለ አድራሻ የሚገልጹ ተቀባይነት የሚኖራቸው የኮሙኒኬሽን ሠነዶች ከሚከተሉት ድርጅቶች መሆን አለበት፡-
  - የገንዘብ ተቋማት (ማለት፡- ባንኮች፣ የመድን/የኢንሹ ራንስ ድርጅቶች፣ ወ.ዘ.ተ)
  - የመገልገያ/ዩቲሊቲ ኩባንያዎች (ማለት፡- የስልክ፣ የውኃ፣ የመብራት ወ.ዘ.ተ)
  - መንግስታዊ ማለት፡- (ፌደራል፣ ስቴት፣ የአካባቢ)
  - የጤና ድርጅቶች
  - የኃይማኖት ተቋማት
  - አትራፊ ያልሆኑ/የማህበረሰብ ድርጅቶች
- በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ያልሆኑ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እየከፈሉ ለማስተማር ተማሪ ለማስ መዝገብ የሚፈልጉ፥ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የዓለም አቀፍ ተማሪዎች መቀበያ እና መመዝገቢያ ጽ/ቤትን "MCPS International Admissions and Enrollment office" በስልክ ቁጥር፡- 240-740-4500 ማነጋገር አለባቸው።
- ቤት አልባ ከሆኑ፣ እባክዎ "MCPS Enrollment Information/Homeless Children web page" ይመልከቱ ወይም "MCPS Homeless Liaison" ስለ ቤት አልባ ጉዳይ የሚመለከተውን 240-740-4511 ደዉለው ያነጋግሩ።

የማስረጃ ሠነዶቹ በወላጅ/ሞግዚት ስም የሆነ እና "MCPS Form 335-74" የተጠቀሰውን አድራሻ የሚያመለክት፣ የላኪውን ድርጅት ስም የያዘ እና ከ 90 ቀን ያላለፈ መሆን አለበት።

### የክትባት ማስረጃ

- የሜሪላንድ የጤና ዲፓርትመንት (MDH) Form 896፣ የሜሪላንድ የክትባት ሠርተፊኬት/Maryland Immunization Certificate (ገጽ 23 ይመልከቱ)
- ፈቃድ ካለው የጤና አገልግሎት ሰጪ ጽ/ቤት የተሰጠ የሰነድ ማስረጃ። በስቴት ህግ መሠረት፥ ወደ መዋዕለህፃናት ለመግባት ምን ዓይነት ክትባቶች እንደሚያስፈልጉ ለማወቅ ፈቃድ ያለው/ያላት የእርስዎን የጤና ተንከባካቢ ያማክሩ ወይም ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የደምበኞች አገልግሎት ማዕከል ቁጥር፡- “311” ይደውሉ። ልጆች ክትባት ካልወሰዱ ከት/ቤት ይወገዳሉ። ልዩ አስተያየት የሚደረገው በህክምና ወይም በሃይማኖት ምክንያት ብቻ ነው። ለት/ቤት ተፈላጊ ክትባቶች እና የሜሪላንድ የክትባት የምስክር ወረቀት https://phpa.health.maryland.gov/OIDEOR/IMMUN/Pages/back-to-school-immunization-requirements.aspx ላይ ይገኛል እናም ከ MCPS ድረገጽ፣ MDH 896ን ይፈልጉ።

## የልጅዎን ጤንነት መጠበቅ

በእያንዳንዱ ት/ቤት የጤና ክፍል የት/ቤት የማህበረሰብ ጤና ነርስ (SCHN)፣ ወይም የት/ቤት ነርስ፣ እና የት/ቤት የጤና ክፍል ቴክኒሻን (SHRT) ተመድቦላቸዋል። "SHRT" ማለት በእያንዳንዱ ት/ቤት የተመደበ(ች) ሰርተፊኬት ያለው/ያላት ረዳት ነርስ በት/ቤት ውስጥ ተማሪዎች ሲታመሙ ወይም የአካል ጉዳት ሲደርስባቸው የመጀመሪያ እርዳታ የሚሰጡ እና መድሃኒት የታዘዘላቸው ተማሪዎች በትክክል እንደሚወስዱ የሚያከታተሉ ናቸው። የት/ቤቱ ነርስ፣ ሪጅስተርድ ነርስ፣ እንደአስፈላጊነቱ ግላዊ የጤና እንክብካቤ እቅዶችን ለማዳበርና ለመተግበር የሁሉን ተማሪዎች ፍላጎቶች ይገመግማል/ትገመግማለች እናም ከቤተሰብ፣ ከት/ቤት፣ እና ከህጋዊ የጤና አገልግሎት ሰጪ ጋር በመተባበር ይሰራል/ትሰራለች። የት/ቤት ነርስ ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ት/ቤቶች ይመደባል/ትመደባለች።

የትምህርት ቤት ነርስ በት/ቤት፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት፣ እና በተማሪው(ዋ) ፈቃድ ያላቸው የጤና አገልግሎት ሰጪዎች መካከል የጤና ጉዳዮችን በሚመለከት አገናኝ ነው/ነች። ተገቢውን ማመቻቸት ይቻል ዘንድ የጤና ችግር ስጋት ካለ ከነርስ ጋር መነጋገር አስፈላጊ ነው።

ወደ መዋእለ ህፃናት በሚገባበት/በምትገባበት አመት ለልጅዎ የማየትና የመስማት ምርመራ ለማድረግ ቀጠሮ ይያዝለ(ላ)ታል። የማጣሪያ ውጤቱን እና ተጨማሪ የመስማት ወይም የእይታ ምርመራ የሚያስፈልግ ከሆነ ፈቃድ ያለው የጤና ባለሙያ መጠየቅ እንዳለብዎት ማሳሰቢያ ይደርሰዎታል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጃቸው በማየትና በመስማት ምርመራ እንዲ(ድት)ሳተፍ የማይፈልጉ ከሆነ የፅሁፍ ጥያቄ ገቢ ማድረግ አለባቸው። ስለ ልጆች የማየት እና የመስማት ችግር፣ ሪሶርሶች፣ እና የማየት እና በትምህርት ቤት የመስማት ምርመራን በሚመለከት መረጃ ለማግኘት ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- https://www.montgomerycountymd.gov/HHS-Program/PHS/SchoolHealth/HearingVision.html።

የእርስዎ ልጅ (በሃኪም የታዘዘለ(ላ)ት ወይም ከካውንተር የተገዛ) መድኃኒት በትምህርት ቤት ቀን መውሰድ ካለበ(ባ)ት ፈቃድ ከተሰጠው-ከተሰጣት ሃኪም የታዘዘ ማስረጃ ለትምህርት ቤት ማቅረብ አለብዎት እና " MCPS Form 525-13" ቅጽ ሞልተው ማቅረብ ይገባዎታል የታዘዘ መድኃኒት ለመስጠት የፈቃድ መስጫ ቅጽ "Authorization to Administer Prescribed Medication" (በልጅዎ ት/ቤት እና በ MCPS ድረገጽ ላይ ይገኛል)። በሃኪም የታዘዘ መድኃኒት በፋርማሲስት ትክክለኛው የመድሃኒት አወሳሰድ መመሪያ የተለጠፈበትን የመድኃኒቱን ኦርጅናል ብልቃጥ/መያዣ ት/ቤት ማምጣት ያስፈልጋል። ያለሃኪም ትእዛዝ ከመደርደሪያ የሚወሰድ መድሃኒት በተመረተበት ኦርጅናል እቃ ላይ በትክክል የተከደነ እና የታሸገ መሆን አለበት። MCPS ቅጽ 525-14፣ አናፊላክሲስ ምርመራ ላለው ተማሪ በድንገተኛ አደጋ ጊዜ እንክብካቤ ለማድረግ፣ ተመራጭ የሆነ በሃኪም ትዕዛዝ የተፈቀደ ራሱ(ሷ) የሚወጋው epinephrine መርፌ። ሁሉም ዓይነት መድኃኒት በወላጅ/በሞግዚት አማካይነት ለት/ቤት በእጅ መሰጠት አለበት። የእርስዎ ልጅ በትምህርት ቤት ቀን ሕክምና የሚያስፈልገው(ጋት) ከሆነ (ለምሳሌ፣ በቱቦ መመገብ፣ ካቲተር) የታዘዘውን መድኃኒት ለትምህርት ቤቱ ማቅረብ አለብዎት እንዲሁም "MCPS Form 525-12" ቅጽ መሙላት ይኖርብዎታል። በህክምና የታዘዘ መድሃኒት የመስጠት ፈቃድ መስጫ ቅጽ "Authorization to Provide Medically Prescribed Treatment" ። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ መሠረት ልጆች ወደ ትምህርት ቤት መድኃኒት ራሳቸው ይዘዉ እንዲመጡ አይፈቀድላቸውም። የአስቸኳይ ጊዜ መድሐኒቶችን በህክምና ባለሙያ የታዘዘበት ፅሁፍ ጋር ሲቀርብ በት/ቤቱ ነርስ ተረጋግጦ ሲጸድቅ ራሳቸዉ ይዘዉ ሊመጡ ይችሉ ይሆናል።

የእርስዎ ልጅ ማናቸውም ዓይነት አስቸኳይ እርምጃ የሚያስፈልግ የጤንነት ችግር ካለበ(ባ)ት ለምሣሌ፡- አስም፣ የስኳር በሽታ፣ የሚጥል በሽታ፣ ተባይ ሲነድፍ ወይም የምግብ አለርጂ ካለበ(ባ)ት እባክዎ ለትምህርት ቤት ርእሰመምህር እና ለትምህርት ቤቱ ነርስ ያሳውቁ እናም "MCPS Form 565-1" ላይ ገልጸው ይጻፉ፣ የተማሪ ድንገተኛ መረጃ "Student Emergency Information" በዚህ መምሪያ መጽሔት ገጽ 19 ላይ ይገኛል።

## ልጅዎን ከት/ቤት አስቀርተው እቤት ስለማቆየት።

እባክዎ ልጅዎን ከዚህ በታች ባሉት ማንኛውም ሁኔታ ወደ ት/ቤት አይላኩ፡-

- ትኩሳት (100°F ወይም ከዚያ በላይ)
- ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ/ማስታወክ
- የሆድ ህመም
- ተቅማጥ
- የገረጣ ወይም ወዝ አልባ ፊት
- ራስምታት
- ከባድ ሳል
- ጆሮ ደግፍ/የጆሮ ህመም
- ከአፍንጫ የሚወጣ ወፍራም ቢጫ ፈሳሽ
- የጉሮሮ ህመም
- የቆዳ ሽፍታ ወይም ኢንፌክሽን
- ቀይ ወይም ሮዝ አይኖች
- ጉልበት ማጣት ወይም የእንቅስቃሴ መቀነስ

ልጅዎን ወደ ት/ቤት ስለ መላክ ወይም አለመላክ ጥርጣሬ ካለዎት፣ ልጅዎን ቤት ማስቀረቱ የተሻለ ሊሆን ይችላል። 1000°F ወይም ከዚያ በላይ ትኩሳት ያላቸው ልጆች ትኩሳቱ ከለቀቃቸው በኋላ ምንም የትኩሳት ማስታገሻ መድሃኒት ሳይወስዱ ለ 24 ሰዓት ቤት መቆየት አለባቸው። ይህ ጥቅሙ ለልጅዎ ብቻ ሳይሆን፣ ለትምህርት ቤቱ ሌሎች ልጆችና ሰራተኞችም ጭምር እንጂ። ወላጅ/ሞግዚት ልጃቸው ከት/ቤት ቀሪ መሆኑ(ኗ)ን አስቀድመው ለት/ቤት ካላሳወቁ፤ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት እድሜ ላይ ያሉ ልጆች በእያንዳንዱ የመጀመሪያ ቀሪ በሚሆኑበት ቀን 12:00 p.m ላይ ልጃቸው ከት/ቤት ስለመቅረቱ(ቷ) ለወላጆች/ሞግዚቶች ይገለጻል። ት/ቤት ውስጥ የጤና አገልግሎት ክፍል አለ፣ ነገር ግን በአስቸኳይ ሁኔታ ብቻ ወላጅ/አሳዳጊ እስከሚደርስ ካልሆነ በስተቀር የታመመ(ች) ልጅ ከአጭር ጊዜ በላይ በት/ቤት ማቆየት አይቻልም። ወላጆችን/ሞግዚቶችን በድንገተኛ ጊዜ ለማግኘት ካልተቻለ "MCPS Form 565-1" ቅጽ ላይ እንደተገለጸው የተፈቀደለትን ሰው ለትምህርት ቤት መግለጽ እንዳለባቸው እናሳስባለን፣ ስለ ተማሪ የድንገተኛ ጊዜ መረጃገጽ 19 ላይ ይመልከቱ) ራሳቸው የታመመ(ች) ልጃቸውን ለመውሰድ የማይችሉ ከሆነ።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ የትምህርት ቤት መግቢያ የጤና መስፈርቶች—በትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች

ለልጃችሁ ምርጥ ትምህርት ለመስጠት እንዲቻል፣ የት/ቤት ሰራተኞች ልጃችሁ ልዩ የጤና ወይም የእድገት ችግር ካለበ(ባ)ት ማወቅ ያስፈልጋቸዋል። የአንድ ተማሪ የጤንነት ሁኔታ ዶኩመንት ከዚህ በታች እንደተገለፀው አስፈላጊ ነው።

## የአካል ምርመራ

በሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ ለመጀመርያ ጊዜ የሚገቡ፣ ወይም ከሜሪላንድ ውስጥ ወይም ውጭ ከሚገኙ የግል ት/ቤቶች የሚዛወሩ፣ ተማሪዎች አካላዊ ምርመራ እንዲወስዱ ያስፈልጋል። ህጉን ለማክበር፣ የአካላዊ ምርመራው ከምዝገባ ዘጠኝ ወር በፊት ወይም ከምዝገባ ስድስት ወር በኋላ መከናወን አለበት። የእርስዎ ልጅ የጤንነት መረጃ መቅረብ ያለበት በ "MCPS Form SR-6" ቅጽ ላይ ሲሆንየሜሪላንድ ትምህርት ቤቶች የአካል ምርመራ ሪኮርድ- Maryland Schools Record of Physical Examination፥ እንደአስፈላጊነቱ ለትምህርት ቤት ሠራተኛ ብቻ ተደራሽ ይደረጋል።

የጤና ኢንሹራንስ ሽፋን የሌላቸው ልጆች ለሜሪላንድ የልጆች ጤና ፕሮግራም (MCHP) ወይም ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የልጆች እንክ ብካቤ ፕሮግራም (CFK) ብቃት ሊኖራቸው ይችላል። ሁለቱም ፕሮግራሞች በሽታ የመከላከል ምርመራዎች፣ የህመምተኛ እንክ ብካቤ፣ እና ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። ለ MCHP ወይም CFK ለማመልከት እርዳታ ከፈለጉ፣ እባክዎ ለብቁነት ምልመላና የድጋፍ አገልግሎት ጽ/ቤት "Office of Eligibility and Support Services" (OESS) የአድራሻዎን ዚፕ ኮድ በመጠቀም ይቃኙ። ድንገተኛ ላልሆነ ጉዳይ የመንግስት መረጃ እና አገል ግሎት፣ በእርስዎ አቅራቢያ ያለ የ OESS አድራሻ ለማወቅና ለ OESS ማቅረብ ያለብዎትን የዶኩመንት ዝርዝር ለማወቅ፣ ከእነዚህ የጤና ፕሮግራሞች ወደ አንደኛው ለማስመዝገብ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሥልክ ቁጥር 311 ይደውሉ። እንዲሁም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ድረገጽ በመጠቀም ለ MCHP ማመልከት ይችላሉ። www.marylandhealthconnection.gov/

## የጥርስ ምርመራ

ተማሪዎች በየዓመቱ የጥርስ ምርመራ እንዲደረግላቸው ይመከራል። እባክዎ የእርስዎ የጥርስ ሃኪም/የጥርስ ሃይጂን ባለሙያ "MCPS Form 525-21" ቅጽ እንዲሞላ ያድርጉ፣ Dental Health Form በዚህ መምሪያ መጽሔት ገጽ 21 ላይ ይገኛል፣ እና ወደ ጤና ክፍል ይመልሱት።

## ክትባቶች

የክትባት ሠርተፊኬት (በተለይም MDH Form 896 በዚህ መምሪያ መጽሔት ገጽ 23 ላይ ይገኛል) አግባብነት ካለው ክትባቶች ጋር፣ በምዝገባ ወቅት መሰጠት/መቅረብ አለበት። ለአሁኑ የትምህርት አመት አስፈላጊ የሆኑ ቢያንስ መጠነኛ የክትባት መስፈርቶችን ዝርዝር ለማየት ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- https://health.maryland.gov/phpa/OIDEOR/IMMUN/pages/back-to-school-immunization-requirements.aspx አስፈላጊ ክትባቶች የማይመለከታቸውና ብቸኛ ተቀባይነት የሚኖራቸው—

- የመድሃኒት ያለመስማማትን የሚገልጽ ፈቃድ ባለው/ባላት የህክምና ባለሙያ የተረጋገጠ ማስረጃ፣
- በሃይማኖት ምክንያት ነፃ ለመሆን ከወላጅ/አሳዳጊ የሚቀርብ ሠነድ፣
- በጊዜያዊ ሁኔታ ምክንያት የመድኃኒት/የህክምና ተአቅቦ ማድረጊያ ሰነድ— በተከታታይ ከሚወሰድ የክትባት መጠን የሚቀጥለውን ለመውሰድ ጊዜው ያልደረሰ በመሆኑ፣ወይም
- ክትባት ለመውሰድ የህክምና ቀጠሮ ማረጋገጫ ወይም የክትባት ሰነድ ከምዝገባ በ 20 የካላንደር ቀኖች ውስጥ (ሰነድ ካልቀረበ ተማሪዎች በቀጠሮው ቀን ማግስት ይገለላሉ)።

ወላጆች/ሞግዚቶች Maryland MyIR በቀጥታ "ImmuNet" የልጃቸውን ክትባት ሪኮርዶች ለማየት መመዝገብ ይችላሉ። ከኦክ ቶበር 2019 ጀምሮ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎች የሚሰጡትን ክትባቶች መረጃ በጠቅላላ በ "ImmuNet" የሜሪላንድ የክትባት መረጃ ሲስተም ውስጥ መመዝገብ አለባቸው። በርካታ የጤና እንክ ብካቤ ሰጪዎች ለእርስዎ ልጅ ቀደም ሲል የተሰጡ ክትባቶችን መረጃ በዚህ ነፃ የድረገጽ ሲስተም ውስጥ አስገብተው ሊሆን ይችላል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብዓዊ አገልግሎቶች ክፍል ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች ለሚገኙና ከሚከተሉት አንዱን የብቁነት መመዘኛዎች ለሚያሟሉ በሦስት ክሊኒኮች ብቻ በቀጠሮ ክትባቶችን የሚሰጥ ሲሆን፡-

- Medicaid (MA፥ MCHP፥ CFK ወዘተ) ተመዝግበዋል
- የግል የጤና ኢንሹራንስ የለውም/የላትም/የላቸውም
- በአነስተኛ ሽፋን ኢንሹራንስ አለው/አላት/አላቸው (ክትባትን አይሸፍንም)

### ክሊኒክ የሚገኙባቸው ቦታዎች:-

School Health Services Center at the Rocking Horse Road Center
4910 Macon Road, Rockville, MD 2085
ቀጠሮ ለመያዝ በዚህ ስልክ ቁጥር ይደውሉ (240)740-4430
(እድሜአቸው ከ 3 እስከ 18 ዓመት ልጆች ብቻ)
Dennis Avenue Health Center
2000 Dennis Avenue፣ Silver Spring፣ MD 20902
ቀጠሮ ለመያዝ (240) 777-1050 ይደውሉ

Germantown Health Center
12900 Middlebrook Road, Germantown, MD 20874
ቀጠሮ ለመያ (240) 777-3380 ይደውሉ

Silver Spring Health Center
ሲልቨርስ ስፕሪንግ ጤና ጣቢያ
8630 Fenton Street, Silver Spring, MD 20910
ሪፈር ከተደረጉ ቀጠሮ ለመያዝ (240) 777-0311 ይደውሉ
(https://www.montgomerycountymd.gov/HHS-Program/PHS/PHSImmunizations-p275.html)

## ሊድ (Lead)

የደም ውስጥ ሊድ/ዕርሳስ ምርመራ ሠርተፊኬት/Blood Lead Testing Certificate (DHMH 4620)፣ መቅረብ አለበት፥ በዚህ የመምሪያ መጽሔት ገጽ 25 ላይ ይገኛልወደ ልዩ ትምህርት ቅድመ መዋዕለህፃናት ፕሮግራሞች፣ ለመዋእለህፃናት፣ ወይም አንደኛ ክፍል ለሚገቡ ተማሪዎች። የ ሄድ ስታርት፣ ቅድመ መዋእለ ህጻናት ተማሪዎች፣ እና በጃኑወሪ 1፣ 2015 ወይም በኋላ ለተወለዱ ልጆች በሙሉ "DHMH Form 4620" ቅጽ ተሞልቶ መቅረብ አለበት (ወይም ልጁ-ልጅቱ "lead" እንደሌለ በ(ባ)ት የደም ምርመራ ውጤት ኤሌክትሮኒክስ ሪፖርት) መቅረብ አለበት፤ ይኼውም ልጁ/ልጅቱ በ12 ወራት ጉብኝት ወቅት "lead" እንዳልተመረዘ(ች) የደም ምርመራ እንደተደረገ እና/ወይም እንደገና በ24 ወራት ጉብኝት ወቅት የደም ምርመራ የተደረገለ(ላ)ት መሆኑን ከሕጋዊ የጤና አገልግሎት ሰጪ የማረጋገጫ ሠርተፊኬት ይቀርባል። (ይህንን ድረገጽ ይመልከቱ፡- https://ww2.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/detail.aspx?recID=303&policyID=JPA-RB§ionID=10)

## የሳንባ ነቀርሳ

ከዩናይትድ ስቴትስ ውጪ ከማናቸውም አገር የሚመጡ ወይም ከ12 ወራት ወይም ከዚያ በላይ ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ ቆይተው ወደ MCPS የሚገቡ ተማሪዎች በምዝገባ ወቅት ከሳምባ ነቀርሳ/tuberculosis ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጫ ሠርተፊኬት እንዲያቀርቡ ይመከራል። በሰውነት ቆዳ ላይ የሳንባ ነቀርሳ/Tuberculosis ምርመራ ለማድረግ በግል የጤና አገልግሎት ሰጪዎች እና በት/ቤት የጤና አገልግሎቶች የክትባት መስጫ ማዕከል (SHSIC) Rocking Horse Road Center, 4910 Macon Road, Rockville, Maryland, የስልክ ቁጥር፡- 240-740-4430 ይገኛል።

# የደህንነት መረጃ

## ደህንነት በቤትና በት/ቤት መካከል፡- በትምህርት ቤት አውቶቡስ መጓዝ

ወላጆች/አሳዳጊዎች ወደ አውቶቡስ ጣቢያ/ማቆሚያ መንገድ ላይ፣ አውቶቡስ ጣቢያ/ማቆሚያ ላይ ፣ እና ከአውቶቡስ ጣቢያ/ማቆሚያ ወደ ቤት ለልጆቻቸው ሃላፊነት አለባቸው። ከአካባቢያቸው ት/ቤት በ1 ማይል ርቀው ለሚኖሩ የኤለመንተሪ ት/ቤት ልጆች የት/ቤት አውቶቡስ አገልግሎት ይሰጣል። የትምህርት ዓመቱ ከመጀመሩ በፊት ት/ቤቶች ስለ አውቶቡስ መስመሮች፣ ሰዓቶች፣ እና አውቶቡሶች ተማሪዎችን ለማሳፈርና ለማውረድ ስለሚቆሙባቸው ስፍራዎች መረጃ ያስተላልፋሉ። ይህ መረጃ በ MCPS ድረ-ገፅ ላይም ይገኛል። ት/ቤት አጠገብ ይኖሩ እንደሆነና በአካባቢያ በዝርዝሩ ውስጥ የመቆሚያ ስፍራ ካልተመዘገበ ልጅዎ ትራንስፖርት የማግኘት እድል ላይኖረው(ራት) ይችላል ማለት ነው። መጓጓዣን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ወደ እርስዎ የትራንስፖርት አስተዳደር ቅርንጫፍ መቅረብ አለባቸው። የትራንስፖርቴሽን ቅርንጫፍ ኃላፊ እንዴት ለማግኘት እንደሚችሉ ከእርስዎ ት/ቤት ወይም ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ድረ-ገጽ ላይ መረጃ ይገኛል።

ልጆች ወደ አውቶቡስ መቆሚያው ከተወሰነው የመውሰጃ ሰዓት ቢያንስ ከአምስት ደቂቃ በፊት መድረስ አለባቸው። ከሰዓት በኋላ ልጆች አንድ ጊዜ ወደ አውቶቡስ ማቆሚያ ከደረሱ በኋላ ኃላፊነቱ የወላጆች ስለሆነ አውቶቡሱ እንደደረሰ በቦታው ለመገኘት ፕላን እንዲያደርጉ፥ ወይም ተረካቢ ሰው፥ ወይም ሌላ አዋቂ ሰው ልጆቹን በሠላም እቤታቸው ወይም ወደ ህፃናት እንክብካቤ ማዕከል ለመውሰድ ኃላፊነት ያለው/ላት ሰው መመደብ አለባቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን ከአውቶቡስ የቱ ጋ እንደሚወርዱ ማስተማር፥ እና ለመጀመርያ ጊዜ አውቶቡስ ከመሳፈራቸው በፊት ልጆች ከአውቶቡስ የሚወርዱበትን ቦታ አሳምረው እንዲያውቁ፣ ከአውቶቡስ መቆሚያ ሥፍራ ወይም ምልክቶች ልዩ ሁኔታ ጋር በደምብ ማስተዋወቅ አለባቸው።

እባክዎ ልብ ይበሉ፡- የአውቶቡስ አሽከርካሪዎች ለተወሰኑ አጭር ቀናት ልጆችን የሚረከቡትን ሁሉን ለማወቅ አይችሉም ይሆናል፥ እና እያንዳንዱን ልጅ ከሚመለከተው አዋቂ/ጎልማሳ ጋር ለማገናዘብ/ለማዛመድ አይችሉም። ተማሪዎች ከአውቶቡስ ሲወርዱ፣ ሙሉ በሙሉ በወላጅ/አሳዳጊ ወይም በሌላ ተንከባካቢ ቁጥጥር ስር ናቸው። ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ተንከባካቢ ከሌለ ወደ ቤት የሚሄዱት በገዛ ራሳቸው ነው። እባካችሁ ልጆቻችሁ ያለ አጃቢ በነፃነት በአውቶቡስ ተጓዦች እንዲሆኑ ከአውቶቡሱ የት መውረድ እንዳለባቸው በትክክል እንዲያውቁ እና፣ ከመውረዳቸው በፊት፥ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም አውቶቡስ ጣቢያ የሚያገኛቸው የሚያውቁትን ሰው ካላዩ የት ቦታ መውረድ እንዳለባቸው ለአውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) እንዲነግሩ ለልጆች ትክክለኛ መረጃ መስጠትዎን ያረጋግጡ። አንዴ ካወቀ(ች)፣ አውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) ተማሪው(ዋ)ን ወደ ት/ቤት ይመልሰዋል/ይመልሳታል፣ ወይም የልጁን-የልጅቱን ደህንነት ለማረጋገጥ ሌላ እርምጃ ይወስዳል/ትወስዳለች።

አብዛኛውን ጊዜ ልጅዎን ከአውቶቡስ መቆሚያው የሚቀበሉ ከሆነና በሆነ ቀን ሊገኙ የማይችሉ ከሆነ፣ ከሚለቀቁበት ሰዓት በታም ቀደም ብሎ ልጅዎ በቀኑ መጨረሻ አውቶቡስ እንዲሳፈር-እንድትሳፈር ከማድረግ ይልቅ መጥተው እንድትወስዱ(ዷ)ት እዚያው ት/ቤት እንዲቆይ-እንድትቆይ እንዲደረግ ለት/ቤት ደውለዉ ይንገሩ። ይህ በጣም በተወሰኑ ባልተጠበቁና ሊወገዱ በማይቻሉ ምክንያቶች ወደ አውቶቡስ መቆምያ ለመድረስ በሚዘገዩበት ጊዜ ብቻ የሚገለገሉበት የአስቸኳይ ሁኔታ መጠባበቂያ እቅድ ነው። ለድንገተኛ ጉዳይ የት/ቤቱን የስልክ ቁጥር በሞባይል ወይም ሌላ አመች ቦታ ላይ ያስቀምጡ። ድንገት ልጅዎ ከሰአት በኋላ አውቶቡስ ማቆሚያ ቦታ ደርሶ(ሳ) እናንተን ወይም ሌላ ተንከባካቢ ካላገኘ(ች) ለልጃችሁ ታላቅ ወንድም/እህት ወይም የክፍል ተማሪ ጋር ጓደኝነት ለመመስረት ፕላን ማድረግ ይመከራል። የአውቶቡስ ፕሮግራሞች ግምታዊ ናቸው ስለሆነም በትራፊክ፣ በአየር ጠባይ ሁኔታ፣ እና በተማሪዎች ለውጥ ምክንያት ሊዘገዩ ይችላሉ። ከመደበኛ የመድረሻ ሰዓት በፊት ቀደም ብሎ ወደ አውቶቡስ ማቆሚያ መድረስ እጅግ አስፈላጊ ነው።

በመጀመሪያው ሳምንት የመዋእለ ህፃናት መምህር ስለ አውቶብስ ደህንነት በዝርዝር ይወያያል/ትወያያለች። አውቶቡስ በመሳፈር፣ በመጓዝ፣ እና በመውረጃ ወቅት የደህንነት ህጎችን ማክበር አስፈላጊ ነው። የደህንነትን ህጎች ከልጅዎ ጋር ሆነው መገምገም የአውቶቡስ ጉዞ ደህንነትን ለማረጋገጥ ያግዛል።

ልጅዎ ከሰዓት በኋላ ከት/ቤት አውቶቡስ ማቆሚያ ወደ ቤት በእግሩ/ሯ ሲጓዝ-ስትጓዝ አዋቂ ሰው አብሮ እንዲሆን የሚፈልጉ ከሆነ፥ የሚከተለውን እንዲያደርጉ እናሳስባለን፡-

- አውቶቡሱ በማንኛውም ቀን ቀደም ብሎ መድረስ ስለሚችል፣ እርስዎ ወይም ሌላ ሰው ከመደበኛ የመድረሻ ሰዓት አስቀድሞ ለመገኘት ማቀድ አለብዎት።
- እርስዎ የማይገኙ ከሆነ ሌላ አዋቂ ሰው እርስዎን በመተካት አውቶቡስ ማቆሚያ ላይ ደርሶ/ሳ ልጅዎን እንዲረከብ/እንድትረከብ በቅድሚያ ፕላን ያድርጉ።
- አስቸኳይ ሁኔታ ካጋጠመዎት እና አውቶቡስ መቆሚያ ለመድረስ ካልቻሉ፣ ልጅዎ አውቶቡስ እንዳይ(ት)ሳፈርና ት/ቤት ቆይቶ/ታ በኋላ እንደሚወስዱ(ዷ)ት፣ ከመሰናበቻ ሰዓት በጣም አስቀድመው ወደ ት/ቤት ደውለው ይንገሩ። ለአስቸኳይ ጊዜ እንዲሆን የት/ቤት ስልክ ቁጥር ሁል ጊዜ ከእርስዎ ጋር ያዙት።
- ልጃችሁ ተገቢውን የአውቶቡስ መቆሚያ መለየቱ(ቷ)ንና ሌላ መቆሚያ ላይ ከአውቶቡሱ መውረድ እንደሌለበ(ባ)ት መገንዘቡ(ቧ)ን አረጋግጡ።
- በእድሜ ታላቅ የሆነ(ች) "ጓደኛ" ተማሪ ወደ ቤት ከልጅዎ ጋር እንዲሄድ-እንድትሄድ ያዘጋጁ፣ ወይም ልጅዎን መውሰድ እስከሚመችዎት ድረስ ልጅዎ በትልቁ(ቋ) ተማሪ ቤት አብረው እንዲቆይ ይፍቀዱ። ይህን ሲያቅዱ ከሌላው(ዋ) ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ጋር አብራችሁ ተነጋጋራችሁ መሆኑን ያረጋግጡ።
- አንድ ነገር "ትክክል ካልሆነ"፣ ልጅዎ ከአውቶቡስ ከመውረዱ(ዷ) በፊት ለአውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) መንገር እንዳ

ለበ(ባ)ት እንዲያውቅ-እንድታውቅ አስረግጠው ይንገሩ። ይህ ማለት አብዛኛውን ጊዜ አውቶቡስ መቆሚያ ላይ የሚገኝ/የምትገኝ አሁን ግን ያ ወላጅ/አሳዳጊ በአውቶቡስ ማውረጃ ቦታ ላይ ካልተገኘ (ች)፥ ወይም መቆሚያውን ከሳተ(ች)፥ ወይም በስህተት ሌላ አውቶቡስ ላይ ቢሳፈር ማንኛውንም መቆሚያ ወይም የሚታወቅ አዋቂ የማያገኙትን ያካትታል።

ተማሪው(ዋ) አንዴ ከአውቶቡስ ከወረደ(ች) በኋላ፣ክትትል ማግኘቱ(ቷ)ን ማረጋገጥ የሚችሉት እርስዎ ብቻ ነዎት።

## በእግር ወደ ት/ቤት መሄድ

አዋቂ የመንገድ ማቋረጫ አስተናጋጆች እና የተማሪዎች ደህንነት ጠባቂዎች በጣም እንቅስቃሴ በሚበዛባቸው የመንገድ ማቋረጫ ዎችና በተወሰኑ ት/ቤቶች ጠዋትና ከሰዓት በኋላ በስራ ላይ ናቸው። ልጆችዎ የእግር መንገድ ህጎችን እንዲከተሉና በስራ ላይ ካሉት አስተናባሪዎች የሚሰጡትን መመርያዎች እንዲያከብሩ አስተም ሯቸው። የመዋእለ ህፃናት ልጅ ምን ጊዜም ቢሆን ብቻው(ዋን) በእግር መሄድ የለበትም/ባትም። ከወላጅ/ሞግዚት፣ ተንከባካቢ፣ ወንድም-እህት፣ ጓደኛ፣ ወይም በእድሜ ትልቅ ከሆነ(ች) ተማሪ ጋር መራመድ/መጓዝ ይመከራል። ልጅዎን አዋቂ የማይሸኘው-የማይሸኛት ከሆነ፣ ከት/ቤት እና ወደ ት/ቤት በእግር የሚያደርስ የሚሻል መንገድ ያሳዩ(ዋ)ት። የትራፊክ ሁኔታ፣ የመስቀለኛ መንገድና ዙርያውን በደንብ የሚታይበት ሁኔታ፣ የማቋረጫዎች/መሻገሪያዎች አጠቃቀም፣ እና ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን ማገና ዘባቸውን ያረጋግጡ። ት/ቤት ከመጀመሩ በፊት ከልጅዎ ጋር በዚህ መንገድ ጥቂት ጊዜ በእግር እየተጓዙ ያለማምዱ(ዷ)ት። መልካም የደህንነት ጥንቃቄዎችን ካለማመዱ በኋላ ልጅዎም በትክክል ዬት እንደሚሄድ-እንደምትሄድ ማወቁን-ማወቋን እርግጠኛ ይሁኑ። ልጅዎ ከእርስዎ ጋር የተለማመደ(ች)ውን መንገድ ይዞ(ዛ) በቀጥታ ወደ ት/ቤት መሄድና ከትምህርት ቤት በኋላ በቀጥታ ወደ ቤት መምጣት አስፈላጊ መሆኑን ያሳምኑ(ኗ)ት።

ልጆችን የማያስጋ የእግር ጉዞ ልምምድ በልጅነታቸው ማስተማር፣ ምንም እንኳን ብቻቸውን ባይሄዱም፣ ለበስተኋላ ዘመናት ለብቻ ቸውም ሆነ ከጓደኞቻቸው ጋር ሲጓዙ በጥንቃቄ የእግር ጉዞ ልምድ ለመገንባት ያግዛቸዋል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጃቸው እነሱ በሌሉበት ወቅት ቤት ሲደርስ-ስትደርስ ምን ማድረግ እንዳለበ(ባ)ት የሚገልጽ መጠባበቂያ ፕላን ማዳበር አለባቸው። ብቻቸውን ወይም ከትልልቅ ልጆች ጋር ወደ ቤት ሲሄዱ፣ እንደዚህ አይነቱን ሁኔታ ለመቋቋም የሚያስችል የአስቸኳይ ሁኔታ ፕላን ያስፈልጋል።

# የኤለመንተሪ መድብለ ቋንቋ (ኢመርዥን) ፕሮግራም

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የኤለመንተሪ መድብለ ቋንቋ (ኢመርሽን) ፕሮግራም (MCPS Elementary Language Immersion Program) ሌላ ቋንቋ ለመማር ፍላጎት ለሚኖ ራቸው ተማሪዎች ልዩ የሆነ አማራጭ ፕሮግራም ነው። እነዚህን ፕሮግራሞች የያዙ ሰባት የኤሌሜንተሪ ት/ቤቶች እና አራት የመካ ከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች አሉ። በመዋእለ ህፃናት ይጀመራል እናም እስከ 8ኛ ክፍል ይቀጥላል።

## በየትኞቹ ቋንቋዎች ትምህርት ይሰጣል?

በእነዚህ መድብለ ቋንቋዎች የሚሰጡት ሦስቱ ቋንቋዎች፥ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ እና ስፓንሽኛ ሲሆኑ አንዳንዶቹ በከፊል አንዳንዶቹ ደግሞ በሙሉ የሚሰጡ ናቸው። በከፊል የሚሰጡት ፕሮግራሞች ሁለት ይዘት አላቸው (ይኼውም፡- ሂሳብ እና ሳይንስ) በቋንቋው ትምህርት ይሰጣል፣ ሙሉ ፕሮግራሞች አራት ይዘት አላቸው (ይኼውም፡- ሂሳብ፣ ሳይንስ፣ ምንባብ፣ እና ማህበራዊ ጥናቶች) በቋንቋው ትምህርት ይሰጣል። ተማሪዎች የተቀሩትን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥርዓተ ትምህርት በእንግሊዝኛ ይማራሉ።

## ልጄ እንዴት መሣተፍ ይችላል/ትችላለች?

እያንዳንዱ ፕሮግራም የቦታ ውስንነት ስላለው፣ ተማሪዎች የሚጋበዙት በእጣ ነው። እጣ/ሎተሪ ለመግባት፣ ወላጆች/ሞግዚቶች የሚከተለውን የቋንቋ ኢመርሽን ድረ-ገጽ መክፈት አለባቸው፡- www.montgomeryschoolsmd.org/immersion ወይም (MCPS Division of Consortia Choice & Application Services) በስልክ ቁጥር፡- 240-740-7800 ይደውሉ። የመዋእለ ህጻናት ተማሪዎች እንዲሁም ማናቸውም ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አዲስ የሆኑ ተማሪዎች፣ ለፕሮግራሙ ከማመልከታቸው በፊት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተማሪ መታወቂያ አስፈላጊ ስለሆነ፥ 2025-2026 የትምህርት ዓመት በአካባቢያቸው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ቀደም ብለው የተመዘገቡ መሆን አለባቸው። ተማሪዎች ከፌብሩዋሪ ጀምሮ የኢመርዥን መመዝገቢያ ቀነ-ገደብ ኤፕሪል 11/2025 ድረስ በሚካሄደው የዕጣ/ሎተሪ ሂደት መግባት አለባቸው። ወላጆች/ሞግዚቶች ሜይ - አጋማሽ ላይ የውጤት መግለጫ ይደርሳቸዋል። ወላጆች/አሳዳጊዎች የፈለጉትን ያህል ለበርካታ የኢመርዥን ፕሮግራሞች ማመልከት ይችላሉ። ለያንዳንዱ ፕሮግራም የትራንስፖርት ሁኔታ የተለያየ ነው። የኢመርዥን ፕሮግራም ቀነ-ገደብ ካለፈ በኋላ ለማመልከት የሚፈልጉ ወላጆች/ሞግዚቶች በመጠባበቂያ ዝርዝር መጨረሻው ላይ በተጠባባቂነት ይመዘገባሉ።

የመድብለ ቋንቋ (ኢመርዥን) ፕሮግራሞቹ በካውንቲው ውስጥ በሚከተሉት ሰባት ቦታዎች ይሰጣሉ፡-

- በርነት ሚልስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ስፓንሽ (በሙሉ)
- ሜሪቨል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፈረንሳይኛ (በሙሉ)
- ፖቶማክ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ቻይንኛ (በከፊል)
- ባያርድ ረስቲን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ቻይንኛ(በከፊል)
- ሮክ ክሪክ ፎረስት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ስፓንሽ (በሙሉ)
- ስላይጎ ክሪክ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፈረንሳይኛ (በሙሉ)
- ዊሊያም ቴይለር ፔጅ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ስፓንሽኛ (በሙሉ)

በራሪ ወረቀቱ ላይ ስለሚገኘው መረጃ ወይም በተደጋጋሚ ስለሚነሱ ጥያቄዎች FAQs) የበለጠ መረጃ ለማግኘት በዚህ መጽሔት ገጽ 27–29 ይመልከቱ (ወይም ይህንን ድረገጽ ይጎብኙ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/admissions/immersion.aspx ወይም Division of Consortia Choice and Application Program Services (DCCAPS) በስልክ ቁጥር 240-740-7800 ይደውሉ።

በተጨማሪም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በስድስት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሁለትዮሽ ቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራሞችን (Two-Way Language Immersion programs) ይሰጣል። የሁለትዮሽ ኢመርሽን ፕሮግራሞች የአካባቢ ትምህርት ቤታቸው ከሚከተሉት ትምህርት ቤቶች አንዱ ለሆነ ተማሪዎች ብቻ ክፍት በመሆናቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራሞች ሎተሪ ውስጥ አልተካተቱም።

- ብራውን ስቴሽን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
- ጌትስበርግ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
- ኬምፕ ሚል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
- ኦክላንድ ተራስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
- ሮሊንግ ተራስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ዋሽንግተን ግሮቭ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት

## ፓረንት አካደሚ/Parent Academy

ልጅዎ እንዴት እርዳታ እንደሚደረግለ(ላ)ት በርካታ ጥያቄዎች ሊኖርዎት ይችላል፡-

- ልጄ የቤት ስራው(ዋ)ን አሟልቶ(ታ) መሥራት እንዲችል-እንድትችል እንዴት ማገዝ እችላለሁ?
- በትምህርት ቤት ልጄ እንዲማር/እንድትማር የሚረዱ የመማር ክህሎቶች ምን ምን ናቸው?
- እንዴት ነው ከልጄ መምህራን ጋር የምገናኘው እና ለልጄ በአለኝታነት የምቆመው?

የፓረንት አካደሚ "Parent Academy TO GO" የተነደፈው ወላጆች ስለልጆቻቸው ትምህርት አቀንቃኞች እና አጋሮች እንዲሆኑ ለማነሣሣት እና ለማስቻል ነው። MCPS ሰራተኞች እና የማህበረሰብ አጋሮች በሚስተናገዱበት የተለያዩ የትምህርት እድሎች፣ ከቤተሰቦች እና ከማህበረሰቡ ጋር ያለንን ተሳትፎ ለማጠናከር ተስፋ እናደርጋለን። ከእያንዳንዱ(ዷ) ስኬታማ ተማሪ ጀርባ ተማሪዎቻችንን በማስተማር ቀልጣፋ ሚና ያላቸው ድጋፍ የሚሰጡ ቤተሰቦች፥ አስተማሪዎች፥ የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ እና የማህበረሰብ አባላት መኖራቸውን እንገነዘባለን።

አሁን ቤተሰቦች በቤታቸው የሚከታተሉት "Parent Academy TO GO" የተሰኘ የወላጅ አካዳሚ ተከታታይ ቨርቹዋል ወርክሾፖችን እንሰጣለን። የእኛ ቨርቹወል አውደጥናቶች የሚያካትቱት በምርምር ጥናት ላይ የተመሠረቱ ስትራቴጂዎች እና የሪሶርስ ክፍልፋዮች፥ ቤተሰቦች የልጆቻቸውን ትምህርት ለመርዳት የሚያስችላቸውን ጥልቅ እውቀት ለመገንባት መማር እና የመለማመድ እድል ይሰጣቸዋል።

የእኛ ቨርቹወል ጭውውት/ውይይት ቤተሰቦች ከ MCPS ሠራተኞች፥ ከአእምሮ ጤና ኤክስፐርቶች፥ ከማህበረሰብ አጋሮች፥ እና ሌሎች ተባባሪዎች ጋር ትርጉም ባላቸው ውይይቶች ላይ እየተሳተፉ በአጭር ጊዜ መፍትሔዎችን እንዲማሩ እና ሪሶርሶችን እንዲጋሩ እድል ይሰጣቸዋል።

ሁሉም ቨርቹወል ሁነቶች ነፃ ናቸው፥ በቅድሚያ መመዝገብ ያስፈልጋል። ከሁነቱ አስቀድሞ ለተሳታፊዎች ከሊንኩ ጋር ኢሜይል ይላክላቸዋል። እባክዎ በዚህ ድረገጽ ላይ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/parentacademy/ ይመዝገቡ። የበለጠ መረጃ ለማግኘት በዚህ የስልክ ቁጥር ለተማሪዎች፣ ለቤተሰብ እና የትምህርት ቤቶች አገልግሎት ይደውሉ 240-740-4620።

## የልጅ እንክብካቤ (Child Care) አመራረጥ

የልጅ እንክብካቤ ሰጪ የሚፈልጉ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወደ LOCATE መደወል ይችላሉ፡- የልጅ እንክብካቤ ሰጪ ሲፈልጉ፥ ስለትምህርት-ዕድሜ ፕሮግራም፣ ስለ ሰመር ካምፕ፣ ስለ ቅድመ መዋዕለ ህፃናት፣ እና/ወይም የህጻናት መዋያ/ነርሰሪ ፕሮግራም ፈቃድ ያለው/ያላት ተንከባካቢ (Child Care) ለማፈላለግ የነፃ አገልግሎት መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር፡- 1-877-261-0060 ይደዉሉ። LOCATE፣ የእንክብካቤ ሰዓቶችን፣ ቦታ፣ የልጆች ብዛትና እድሜ፣ እና የልጅ እንክብካቤ ዋጋ በመሰሉ፣ በእያንዳንዱ ቤተሰብ ፍላጎቶች ላይ በመመስረት አገልግሎት ሰጪዎችን ለይቶ ይገልጻል። ይህን አገልግሎት በበርካታ ቋንቋዎች ማግኘት ይቻላል።

ለትምህርት ቤት እድሜ ለደረሱ ልጆች፣ LOCATE በት/ቤቱ አካባቢ ወይም በአካባቢው አገልግሎት የሚሰጡትን መለየት ይችላል። በተጨማሪ፣ አማካሪዎች መልካም ፕሮግራሞችን ስለ መለየት ጥቆማዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ትክክለኛ ፕሮግራም ለልጃቸው እንዲመርጡ ለማገዝ ለክትትል ቀላል የሆኑ ጥቆማዎችን ይሰጣሉ። መጠቆሚያ/LOCATE የልጆች እንክብካቤ/Child Care በሜሪላንድ የትምህርት ዲፓርትመንት በቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ሰጪዎችንና የልጆች እንክብካቤ ማእከሎችን (የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት የልጆች እንክብካቤ ጽ/ቤት) ተቀባይነት ያላቸውን ሁለቱንም ለይቶ ያሣያል።

ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚከተሉትን ባህርዮች የሚያንፀባርቁ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ፕሮግራሞች ማግኘት አለባቸው፡- ሰራተኛው/ዋ የልጆቹን እድገታዊ ፍላጎቶች የሚገነዘብ-የምትገነዘብ፤ ፕሮግራሙ የተለያዩ ትምህርታዊ ቁሳቁሶች ያሉት፣ አቅርቦቶች፣ እና ከተገልጋዮች እድሜ ጋር አግባብ የሆኑ መጫወቻዎች ያሏቸው፤ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች መልካም አቀባበል ያላቸውና የሚያሳትፉ፤ መርሃግብሮችን፣ ፖሊሲዎችን፣ እና ፕሮግራሞችን በሚመለከት ሰራተኛው(ዋ) ከት/ቤት ባልደረቦች ጋር በትብብር አብረው የሚሠሩ።

የስቴት እና የካውንቲ ህጎች ድንጋጌ መሠረት ከ8 አመት በታች የሆኑ ልጆች ሁልጊዜ በወላጅ/አሳዳጊ፣ የልጅ ተንከባካቢ፣ ወይም ቢያንስ 13 አመት እድሜ ባለው/ባላት ልጅ ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ ይደነግጋሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ልጅ እንክብካቤ መረጃዎችን በዚህ ድረገጽ ላይ መፈለግ ይችላሉ፡- www.marylandfamilynetwork.org

## ት/ቤት የሚዘጋበት ወቅት

አንዳንድ ጊዜ የትምህርት ሰዓትን ማዘግየት ወይም በዚያ ቀን ትምህርት ያለመኖር፣ ወይም ተማሪዎችን ቀደም አድርጎ ወደ ቤታቸው መላክ የሚያስፈልግበት ወቅት ይኖራል። የት/ቤት የስራ ፕሮግራም መለወጥ የሚያስፈልግበት ዋና ምክንያት የልጆች ደህንነት ነው። የአየር ጠባይ መጥፎ በሚሆንበት ወቅት፣ የት/ቤቶች መዘጋት ወይም መዘግየት የሚገለጹበት በርካታ መንገዶች አሉ። በዕለቱ ትምህርት ቤት የሚሰረዝ፣ ዘግይቶ የሚጀመር፣ ወይም ተማሪዎች ቀደም ብሎ የሚሰናበቱ ከሆነ፥ MCPS ድረገጽ፣ MCPS X አካውንት (x.com/MCPS)፣ MCPS ፌስቡክ አካውንት እና MCPS TV (ቻነል 34 ኮምካስት ላይ፣ 36 ቨራይዘን ላይ፣ እና 89 RCN ኬብል)ላይ መልእክት ይተላለፋል። በተጨማሪ፡- MCPS የኢ-ሜይል መልእክቶችን Connect-ED (ከወላጆች/አሳዳጊዎች የተሰጡ ስልክ ቁጥሮችን እና የኢሜይል አድራሻዎችን የያዘ በድምፅ የተቀዳ የስልክ እና የኢሜይል መልእክት ይልካል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የስራ ሁኔታ እና የትምህርት ቤቶች በአስቸኳይ ሁኔታ ወይም በአደጋ ጊዜ የሚዘጋበትን ኮድ ለማወቅ ይህንን አውታረመረብ/ሊንክ በመጠቀም ማግኘት ይቻላል። https://www.montgomeryschoolsmd.org/emergency/closings/. በተጨማሪም የቴክስት እና ኢሜይል መልእክቶችን በካውንቲው የማስጠንቀቂያ ሲስተም እንዲደርስዎት (ለመመዝገብ፣ የሚቀጥለውን ድረገጽ ይጎብኙ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/emergency/alertmcps.aspx). በተጨማሪ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በተቀዳ ድምፅ የሚተላለፍ መልእክት ለመስማት በስልክ ቁጥር፡- 301-279-3673 ለመደወል ይችላሉ። የመዘጋት መረጃዎች በአካባቢ ሬድዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎችም ይነገራሉ።

ስለ ት/ቤት መዘጋት እና ዘግይቶ የሚከፈት ከሆነ በጣም በጠዋት በ 5:00 a.m መረጃ ይተላለፋል። ት/ቤቶች ቀደም ተብሎ የሚዘጉ ከሆነ በ 11:00 a.m ይገለጻል።

አንዳንድ ጊዜ የውሃ፣ የማሞቂያ፣ ወይም የኤሌክትሪክ ችግሮች ሲከሰቱ አንድን ት/ቤት ሙሉውን ቀን ወይም በከፊል መዝጋት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። በዚህ መልክ ት/ቤቶች የሚዘጉ ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ እያንዳንዱ ት/ቤት ConnectEd በመጠቀም ለወላጆች/ሞግዚቶች ያሳውቃል። እንደዚህ ዓይነት ወይም ሌላ ድንገተኛ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ በፍጥነት ሊገኙ የሚችሉበትን የስልክ ቁጥሮችን እና ኢ-ሜይል አድራሻዎችን በአግባቡ ለልጅዎ ት/ቤት ማሳወቅ አለብዎት።

በተጨማሪም፣ እርስዎን ለማግኘት ባልተቻለ ጊዜ ሌላ ልጅዎን ለመርዳት የሚችል ሰው ለመጥራት እንዲቻል፣ በድንገተኛ ጊዜ ልጅዎን ለመርዳት ከእርስዎ ጋር ፈቃደኛ የሆነ/ች ቢያንስ የአንድ ሰው ስም እና የስልክ ቁጥር ለልጅዎ ት/ቤት መስጠት አለብዎት። መረጃው MCPS ቅጽ 565-1 የተማሪ የድንገተኛ ጊዜ መረጃ ገጽ 15 ላይ ተሞልቶ ለልጅዎ ትምህርት ቤት መቅረብ አለበት። እባክዎን ከእነዚህ መረጃዎች ማናቸውም ለውጥ ከተደረገ ወዲያውኑ ለት/ቤት ያሳውቁ።

## ቅጾች እና ምዝገባ

MCPS ቤተሰቦች መዋዕለ ሕጻናት የሚገቡ ልጆቻቸውን በኦንላይን እንዲያስመዘግቡ እድል ሰጥቷል።

- MCPS ቤተሰቦች ParentVUE አካውንቶችን ወደ ወላጅ ፖርታል ገብተው ልጆቻቸውን ለመዋዕለ ሕፃናት ለማስመ ዝገብ የኦንላይን ምዝገባ አገናኝ ጠቅ በማድረግ፥ ከምዝገባ ዝርዝር ውስጥ 2025-2026 አዲስ ምዝገባ የሚለውን በመምረጥ ማስመዝገብ ይችላሉ።
- "ParentVUE" አካውንት የሌላቸው የ MCPS ቤተሰቦች/ሞግዚቶች የአካውንት መክፈቻ ደብዳቤ ለማግኘት ትምህርት ቤታቸውን መጠየቅ አለባቸው።
- ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አዲስ የሆኑ ቤተሰቦች በኦንላይን ለመመዝገብ/Online Registration system"ParentVUE" አካውንት መክፈት ይችላሉ። (https://md-mcps.edupoint.com/PXP2_OEN_Login.aspx)
- በዚህ መመሪያ ጽሑፍ ውስጥ በተካተተው የወረቀት ቅጽ ማስመዝገብ የሚፈልጉ ወላጆች/አሳዳጊዎች የሞሉትን የማስመ ዝገቢያ ቅጽ ወደ ትምህርት ቤት ማቅረብ ይችላሉ።

የሚከተሉትን ቅጾች በኤሌክትሮኒክስ በመጠቀም ኦንላይን የመዋእለ ህጻናት ምዝገባ ማድረግ ይቻላል። በወረቀት ምዝገባ የሚያደርጉ ከሆነ፥ በዚህ መምሪያ መጽሐፍ ከዚህ በታች የሚገኘው በተማሪው(ዋ) ወላጅ/ሞግዚት የተሞላ ቅጽ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ አለበት፦

- MCPS ቅጽ 560-24፣ የአዲስ ተማሪ መረጃ
- MCPS ቅጽ 345-17፣ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት የቅድመ-መዋእለ ህፃናት ተሞክሮ
- MCPS ቅጽ 565-1፣ የተማሪ ለድንገተኛ ጊዜ የሚሆን መረጃ

ምዝገባ የሚያደርጉት በኤሌክትሮኒክስ ከሆነ፥ የሚከተሉት ቅጾች ታትመው ህጋዊ ፈቃድ ባለው/ባላት የጤና እንክብካቤ ሰጪ አማካይነት ተሞልቶ በተማሪው(ዋ) ኦንላይን ምዝገባ ጋር መያያዝ አለበት። ቅጾቹን ወደ ትምህርት ቤት አዘግይተው ለመመለስ መምረጥም ይችላሉ። ምዝገባውን በወረቀት የሚሞሉ ከሆነ፥ ከዚህ በታች ያሉት ቅጾች ከዚህ የመዋእለ ህጻናት መምሪያ መጽሐፍ ተነጥለው ህጋዊ ፈቃድ ባለው የጤና ባለሙያ ከተሞላ በኋላ ከትም ህርት ቤት የመጀምሪያ ቀን በፊት ወደ ትምህርት ቤት መመለስ አለበት።

- MCPS ቅጽ 525-17፣ ስለ ጥርስ ጤንነት መግለጫ ቅጽ
- MDH 896፣ የሜሪላንድ የጤና ጥበቃ መምሪያ የክትባት ሰርተፍኬት፣ የሜሪላንድ የክትባት ማረጋገጫ፦ MDH 896, Maryland Department of Health Immunization Certificate, Maryland Immunization Certification (https://ww2.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/detail.aspx?formID=442&formNumber=DHMH%20896&catID=2&subCatid=0)
- DHMH 4620 የደም ሊድ/Blood Lead ምርመራ የምስክር ወረቀት፦ (https://ww2.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/dhmh%204620.pdf)

በኤሌክትሮኒክስ የሚሞሉ ከሆነ፥ የሚከተለው ቅጽ ታትሞ "Part I" በወላጅ/ሞግዚት መሞላት አለበት። "Part II" ህጋዊ ፈቃድ ባለው የጤና ባለሙያ አማካይነት ተሞልቶ የኦንላይን ምዝገባ አባሪ ሆኖ መያያዝ እና በወላጅ/ሞግዚት አማካይነት ወደ ትምህርት ቤት መመለስ አለበት። ምዝገባውን በወረቀት የሚሞሉ ከሆነ ቅጹ ከዚህ የመዋእለ ህጻናት መምሪያ መጽሐፍ ተነጥሎ "Part I" በወላጅ/በሞግዚት መሞላት አለበት። ክፍል II በህጋዊ የጤና ባለሙያ ተሞልቶ በወላጅ/አሳዳጊ አማካይነት ወደ ት/ቤት መመለስ አለበት።

- MCPS ቅጽ SR-6፣የሜሪላንድ ት/ቤቶች የአካል ምርመራ ሪኮርድ

2025–26 የትምህርት ዓመት የሜሪላንድ ክትባት መስፈርት ገና አልተጠናቀቀም። መስፈርቶቹ ከተጠናቀቁ በኋላ ይህ መረጃ በሜሪ ላንድ የጤና ዲፓርትመንትድረገጽ ላይ ይገኛል።

# ስለ አዲስ ተማሪ መረጃ

Office of Shared Accountability፣ Records Unit
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Rockville, Maryland 20850

*መመሪያዎች፡- ይህ ቅጽ በወላጅ/አሳዳጊ ወይም ቅጹን ለመሙላት ብቃት ባለው/ባላት ተማሪ የሚሞላ ነው። አዲስ ወይም ተመልሰው ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለሚገቡ ተማሪዎች በሙሉ፣ የሚከተሉት ማረጋገጫዎች በምዝገባ ወቀት መቅረብ አለባቸው፡- ቤት አልባ ካልሆኑ በስተቀር፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪነት ማስረጃ፣ ዕድሜ የሚገልጹ እና የክትባቶች ማስረጃዎች።*

**የተማሪ መረጃ**

ከልደት ሠርተፊኬት ወይም ከሌላ የልደት ማስረጃ ጋር መስማማት (አንድ አይነት መሆን) አለበት

ህጋዊ የአያት ስም__________ ህጋዊ የግል/ስም__________ ህጋዊ የአባት ስም __________

ተማሪ የሚታወቅበት-የምትታወቅበት የመጀመሪያ ስም __________

የተወለደ(ች)በት ቀን _____/_____/_____ ጾታ ❑ ወ (ወንድ) ❑ ሴ (ሴት) ❑ X (ያልተገለጸ/non-binary)

የት/ቤት ስም__________ MCPS መታወቂያ#__________ ክፍ_____

**ሜሪላንድ የቤት ቋንቋ መቃኘት/ቅኝት**

በፌደራል እና በስቴት ተፈላጊ እንደመሆኑ መጠን፣ የቤት ቋንቋ ቅኝት በሁሉም ተማሪዎች ላይ ይደረጋል እናም ጠቀሜታው ምናልባት ተማሪ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ድጋፍ ያስፈልገው(ያስፈልጋት) እንደሆነ ለመወሰን ነው።እና ለስደተኝነት ጉዳይ ወይም ለስደት ጉዳይ ሃላፊዎች ሪፖርት የማድረግ ጥቅም ላይ አይውልም።

ከዚህ በታች ባሉት ሦስት ጥያቄዎች ሁለቱ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ሌላ ተጠቅሶ ከሆነ፣ ተማሪው(ዋ) የእንግሊዝኛ ቋንቋ ድጋፍ አገልግሎቶች ያስፈልጉ እንደሆነ ግምገማ-ቅኝት ይደረጋል። ለፈተና ተጨማሪ መመዘኛ ሊታሰብ (ግንዛቤ ውስጥ ሊወሰድ) ይችላል።

ምን ቋንቋ/ቋንቋዎችን ነው ተማሪው(ዋ)በመጀመሪያ ለመናገር የተማረ(ች)ው? __________

ምን ቋንቋ ነውተማሪው(ዋ)በአብዛኛው ለግንኙነት የሚጠቀመው/የምትጠቀመው? __________

በቤትዎ ውስጥ ምን ቋንቋ(ዎች) ይነገራል(ሉ)? __________

**የእድሜ ማረጋገጫ — (የልደት ማስረጃ)የትኛው ሰነድ እንደቀረበ ያመላክቱ/ያሳዩ**

❑ የልደት ሠርተፊኬት ❑ ፓስፖርት/ቪዛ ❑ የሀኪም ሠርተፊኬት ❑ የጥምቀት ወይም የቤተክርስቲያን ሠርተፊኬት ❑ የሆስፒታል ሠርተፊኬት ❑ ወላጆች ዜግነት ያገኙበት ማረጋገጫ

❑ የልደት ምዝገባ ወረቀት ❑ ሌላ የማንነት ፍጋዊ ማረጋገጫ (ይግለጹ) __________

**መኖሪያ**

የመንገድ ስም __________ ከተማ__________ ስቴት____ ዚፕኮድ__________

የኢ-ሜይል አድራሻ __________ ዋናነኛው የቤት ወይም የሞባይል ስልክ ቁጥር_____ - _____ - _____

ሁኔታዎች ( የሚመለከተው/ታት ከሆነ)

- ❑ ቤት አልባ ህፃን(ልጅ)/ብቻው(ዋ)ን የሆነ(ች) ወጣት(MCPS Form 335-77፣ የቤት አለመኖር መግለጫ ይሙሉ)
- ❑ ይፋ ያልተደረገ የዘመድ እንክብካቤ (መደበኛ ያልሆነ ከዘመድ ጋር በመጠጋት እንክብካቤ የሚያገኙ ልጆች MCPS ቅጽ 334-17 ቃለመሃላ መሙላት ያስፈልጋል)
- ❑ በየሜሪላንድ ስቴት ቁጥጥር የሚደረግበት እንክብካቤ (Maryland State Supervised Care) (በሜሪላንድ ስቴት ቁጥጥር የሚደረግበት እንክብካቤ (Maryland State Supervised Care) የልጅ ምዝገባ እና የትምህርት መረጃ/ሪኮርድ ማስተላለፊያ MCPS ቅጽ 560-35 ይሞላ)

የመኖሪያ ማረጋገጫ —MCPS Regulation JEA-RB, Enrollment of Students-ስለ ተማሪዎች ምዝገባ፣ ስለነዋሪነት ማረጋገጫ መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎችን በሚመለከት ከዚህ የሚከተሉት ተቀባይነት ያላቸው ሠነዶችን ይዘረዝራል (ቤታልባ ካልሆነ(ች) በስተቀር፡-

- ❑ ወቅታዊ የንብረት ታክስ የከፈሉበት ማስረጃ ❑ ወቅታዊ የኪራይ ውል ❑የመጀመሪያው የኪራይ ውል አብቅቶ ከሆነ ወቅታዊ የኪራይ ውል የታደሰበት/የተራዘመበት ወይም የማብራት፣ የውኃ መገልገያ የተከፈለበት ማስረጃ
- ❑ የመኖሪያ ቤቱ በጋራ/በደባልነት ከሆነ የማሳወቂያ ቅጽ (MCPS ቅጽ 335-74) መሞላት አለበት።

**የስደተኛ አገልግሎቶች እና ከተወሰኑ ፈተናዎች/ቴስቶችን ማስቀረት/IMMIGRANT SERVICES AND EXEMPTIONS FROM CERTAIN TESTS**

ለስደተኛ አገልግሎቶች ለማግኘት ብቁ መሆንን እና/ወይም ከተወሰኑ ፈተናዎች ነፃ መሆንን ለመወሰን እንዲያግዝ፣ እባክዎ የሚከተሉትን መረጃዎች ያቅርቡ፡-

ተማሪው(ዋ) የተወለደው/ችው ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ ነው? ❑ አዎ ❑ አይደለም አዎ ከሆነ ተማሪው(ዋ) ለምን ያህል ጊዜ በዩ.ኤስ ከመዋዕለ ህጻናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል (U.S. K–12) ትምህርት ቤት ነበር/ነበረች?

ተማሪው(ዋ) ከመዋዕለ ህጻናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል (U.S. K–12) ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ የገባ(ች)በት ቀን _____/_____/_____

**ክትባቶች**

ክትባቶችን የወሰደ(ች)በት ማረጋገጫ —MCPS Regulation JEA-RB፣ ስለተማሪዎች ምዝገባ፣ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ተቀባይነት ያላቸው ሠነዶችን ይዘረዝራል፡-

- ❑ የሜሪላንድ የጤና መምሪያ የክትባት ሰርትፊኬት/Maryland Department of Health Immunization Certificate 896
- ❑ በህክምና ባለሙያ ወይም የጤና ክሊኒክ በኮምፒውተር የተዘጋጀ ፎርም/ቅጽ ❑ሌላ__________

**የዘር ሃረግ**

1. የዘር ሃረግ፡ የሚከተሉትን መግለጫዎች ያንብቡ እና የተማሪው(ዋ)ን የትውልድ ሃረግ በሚገልጸው ላይ ምልክት ያድርጉ።
   ይህ(ች) ተማሪ ሂስፓኒክ ወይስ ላቲኖ ነው/ናት? (አንድ መልስ ይምረጡ።) ❑ አዎ ❑ አይደለም
   የኩባ፣ የሜክሲኮ፣ የፖርቶሪኮ፣ ከደቡብ ወይም መካከለኛ አሜሪካ፣ ወይም ሌላ የስፓንሽ ባህል ወይም ዝርያ ያላቸው፣ ዘራቸው ከየትኛውም ቢሆን ሂስፓኒክ ወይም ላቲኖ ተብለው ይወሰዳሉ።
2. የዘር ሃረግ። የተማሪው(ዋ)ን የዘር ሃረግ በሚያመለክተው ቦታ ላይ ምልክት ያድርጉ። ማንኛውም ዝርያ ቢሆን ቢያንስ አንድ ዘር መምረጥ አለብዎት። ከአንድ በላይ መምረጥ ይቻላል። የዚህ(ች)ን ተማሪ ዘር ያመልክቱ።(የሚመለከተውን ሁሉ ይምረጡ።)
   ❑ አሜሪካዊ/ት ህንዳዊ/ት ወይም የአላስካ ተወላጅ ❑ ኤዥያዊ/ት ❑ ጥቁር ወይም አፍሪካዊ/ት አሜሪካዊ/ት ❑ ከሀዋይ ወይም ሌላ የፓስፊክ ደሴት ተወላጅ ❑ ነጭ

**የበፊተኛው (የቀድሞ) ት/ቤት ተሞክሮ**

ተማሪው/ዋ ከዚህ ቀደም በሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተምሮ/ራ ያውቃል/ታውቃለች? ❑ አዎ ❑ አይደለም

አዎ ከሆነ፡- በመጨረሻ የተከታተለበ(ች)ት የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)______________________________

የተከታተለበ(ች)ት ጊዜ _____/_____/______እስከ _____/_____/______የመጨረሻ ክፍል______

**መጨረሻ የተማረ(ች)በት ት/ቤት ስምና አድራሻ**

______________________________________________________________

ከት/ቤቱ የወጣ(ች)በት ቀን _____/_____/______ የመጨረሻ ክፍል______ ❑ የሕዝብ ት/ቤት ❑ የግል ት/ቤት

**ለተማሪው(ዋ) ሃላፊነት ያላቸው ወላጆች/ሞግዚቶች***

በተማሪው(ዋ) አድራሻ የሚኖር የመጀመሪያ ኃላፊነት ያለው/ያላት ወላጅ/አሳዳጊ፦

______________________________

ዝምድና (ግንኙነት)፡- ❑ እናት ❑ አባት ❑ አሳዳጊ

ቀጣሪ ______________________________

ስልክ #1 _____-_____-______ ስልክ #2 _____-_____-______

ኢ-ሜይል______________________________

ወላጅ የሚመርጡት ቋንቋ፦ ❑ Amh ❑ Chi ❑ Fre ❑ Kor ❑ Por ❑ Spa ❑ Viet

በተማሪው(ዋ) አድራሻ የሚኖር ኃላፊነት ያለው ወላጅ/አሳዳጊ፡-

______________________________

ዝምድና (ግንኙነት)፡- <> እናት<> አባት <> አሳዳጊ

ቀጣሪ ______________________________

ስልክ# 1 _____-_____-______ ስልክ #2 _____-_____-______

ኢ-ሜይል______________________________

ወላጅ የሚመርጡት ቋንቋ፦ ❑ Amh ❑ Chi ❑ Fre ❑ Kor ❑ Por ❑ Spa ❑ Viet

የወላጅ/የሞግዚት ስም (ከዚህ በላይ ከተገለጸው ወላጅ/ሞግዚት የተለየ ከሆነ)፦

______________________________

ዝምድና (ግንኙነት)፡- ❑ እናት ❑ አባት ❑ አሳዳጊ

❑ ሌላ______________________________

አድራሻ ______________________________

ስልክ ቁጥር_____-_____-______

የወላጅ/የሞግዚት ስም (ከዚህ በላይ ከተገለጸው ወላጅ/ሞግዚት የተለየ ከሆነ)፦

______________________________

ዝምድና (ግንኙነት)፡- ❑ እናት ❑ አባት ❑ አሳዳጊ

❑ ሌላ______________________________

አድራሻ ______________________________

ስልክ ቁጥር_____-_____-______

* ❑ የወላጅ/አሳዳጊ ህጋዊ መታወቂያ (ፎቶግራፍ ያለው) እና ከተማሪው(ዋ) ጋር ያለ ግንኙነት የተረጋገጠበት ማስረጃ (ይግለጹ)

ተማሪው(ዋ) በአገልግሎት ላይ የሚገኝበት-የምትገኝበት የጦር ክፍል (ሙሉ ጊዜ) የጦር ኃይል፣ ባህር ኃይል፣ አየር ኃይል፣ የጠፈር ኃይል፣ የባህር ሠርጓጅ ኃይል፣ የጠረፍ ጥበቃ ኃይል፣ ብሔራዊ የመከላከያ ሠራዊት፣ ወይም ተጠባባቂ የጦር ሃይል (ጦር ሠራዊት፣ የዩ ኤስ ብሔራዊ የጥበቃ ኃይል፣ ባህር ኃይል፣ አየር ኃይል፣ የጠፈር ኃይል፣ የባህር ሠርጓጅ ኃይል፣ የዩ ኤስ የአየር መከላከያ ሃይል ወይም የጠረፍ ጥበቃ ኃይል) አባል ነው/ናት? ❑ አዎ ❑ አይደለም

| የወንድም/እህት (ስም) | የትውልድ ቀን | አሁን የሚገኝበት/የምትገኝበት ት/ቤት |
|---|---|---|
| ______________ | _____/_____/______ | ______________ |
| ______________ | _____/_____/______ | ______________ |
| ______________ | _____/_____/______ | ______________ |

**ህጋዊ ውክልና የሌለው/የሌላት ወላጅ (ተግባራዊ ከሆነ)**

ስም ______________________________

አድራሻ______________________________

አሳዳጊን/ተንከባካቢ የሚመለከቱ ጉዳዮች ❑ አዎ ❑ አይደሉም አዎ ከሆነ፣ ት/ቤቱን ያነጋግሩ።

**ሌላ መረጃ**

| | | |
|---|---|---|
| ተማሪው(ዋ) ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP)አለው?/አላት? | ❑ አዎ | ❑ አይደለም |
| ተማሪው(ዋ) ሰክሽን-Section 504 plan አለው?/አላት? | ❑ አዎ | ❑ አይደለም |
| ተማሪው(ዋ) በአሜሪካ ትምህርት ቤት በቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም (LIEP) ELD* አገልግሎቶችን የሚቀበል የመድብለ ቋንቋ ተማሪ (EML) ነው/ነች? አዎ ከሆነ፣ መጀመርያ በዩ.ኤስ ት/ቤት የገባ(ች)በት ቀን ELD* _____/_____/______<br>የለቀቀ(ች) ከሆነ፣ የለቀቀ(ች)በት ቀን/ጊዜ መቼ ነበር? _____/_____/______<br>*ELD–እንግሊዝኛ ቋንቋ ማዳበር/ESOL–እንግሊዝኛ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች/ESL–እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ/ENL–እንግሊዝኛ እንደአዲስ ቋንቋ | ❑ አዎ | ❑ አይደለም |
| ተማሪው/ዋ ከት/ቤት ታግዶ(ዳ) ያውቃል/ታውቃለች?<br>አዎ ከሆነ፣ ተማሪው(ዋ) በዚህ ወቅት ታግዷል?/ታግዳለች? | ❑ አዎ<br>❑ አዎ | ❑ አይደለም<br>❑ አይደለም |
| ተማሪው(ዋ) ከት/ቤት ተባሮ ያውቃል/ተማሪዋ ከት/ቤት ተባራ ታውቃለች?<br>አዎን ከሆነ፣ ተማሪው(ዋ) በዚህ ወቅት ከትምህርት ቤት ተባሯል?/ተባራለች? | ❑ አዎ<br>❑ አዎ | ❑ አይደለም<br>❑ አይደለም |
| የትምህርት አመት ከተጀመረ በኋላ ምዝገባ የሚያደርጉ ከሆነ፣ ዋናው መረጃ ይፋ እንዳይደረግ ይፈልጋሉ?<br>አዎን ከሆነ MCPS Form 281-13፣ Annual Notice for Directory Information and Student Privacy ይሙሉ። | ❑ አዎ | ❑ አይደለም |

በዚህ ቅጽ እና በማናቸውም አባሪ ላይ የቀረቡት መረጃዎች እኔ እስከማውቀው ድረስ ትክክለኛ፣ የተሟሉ እና እውነት ናቸው። እዚህ በቀረበው ማናቸውም መረጃ ላይ ሀሰት ቢገኝበት ላለመቀበል/መከልከል ምክንያት እንደሚሆን እገነዘባለሁ። በተጨማሪ፣ ተማሪው(ዋ) የዚህ ካውንቲ ነዋሪ መሆን ካቆመ/ ካቆመች ለት/ቤቱ ርእሰ መምህር የማሳወቅ ኃላፊነት እንዳለብኝ እና፣ ቤት የለሽ ካልሆነ(ች) በስተቀር፣ በካውንቲው ውስጥ ነዋሪ ላልሆነ(ች)ባቸው ማንኛውም ጊዜያት ላለው የትምህርት ክፍያ ተጠያቂ እንደምሆን እገነዘባለሁ። ተማሪው/ተማሪዋ IEP ካለው/ካላት፣ IEP ቡድን የተማሪው(ዋ)ን ምደባ መወሰን እንዳለበት እረዳለሁ።

በኤሌክትሮኒክስ ሞልቼና ፈርሜ ያቀረብኩት ይህ ቅጽ በግሌ በአካል ቀርቤ እንደመፈረም የሚቆጠር እኩል ዋጋ ያለው መሆኑን ይገባኛል።

______________________________ _____/_____/______

ፊርማ፦ ወላጅ/ሞግዚት ወይም ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ ቀን

**እባክዎን ልብ ይበሉ/ያስተውሉ፡**

**ይህ ቅጽ ለMCPS አትሌቲክስ ተቀባይነት የለውም። ለMCPS አትሌቲክስ ቅጽ SR-8ን መጠቀም አለብዎት።**

# የተማሪ ሪኮርድ ካርድ 6

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE)
የሜሪላንድ ስቴት የጤና ዲፓርትመንት (MDH)
ሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)
Rockville, Maryland

የ MCPS ቅጽ SR-6
January 2020
ከባለ 4 ገጾች 1ኛው ገጽ

## ከወላጆች/ሞግዚቶች የልጃቸውን የጤና ምርመራ ሪኮርድ መጠየቂያ

ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሜሪላንድ የሕዝብ ትምህርት ቤት ለመግባት እንዲችል/እንድትችል፣የሚከተሉትን ማሟላት ያስፈልጋል፡-

- ወደ ት/ቤት ከመግባቱ/ከመግባቷ ከዘጠኝ ወራት በፊት ወይም ስርአቱ ውስጥ ከገባ/ከገባች በስድስት ወሮች ውስጥ በተፈቀደለት የጤና ባለሙያ አማካይነት የአካል ምርመራ መፈፀም አለበት። ይህንን ለማሟላት በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ እና በሜሪላንድ ስቴት የጤና መምሪያ አማካይነት የተዘጋጀ የአካል ምርመራ ቅጽ መጠቀም ያስፈልጋል።
- ከቅድመ-ትምህርት ቤት (ፕሪ ስኩል) ጀምሮ እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ለሚገኙ ሁሉም ተማሪዎች ለተወሰኑ የህፃናት ተላላፊ በሽታዎች መከላከያ ተቀዳሚ/የመጀመሪያ ክትባት ለማጠናቀቃቸው ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል። ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች የMaryland ክትባት ማረጋገጫ ቅጽ ከአቅራቢያ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች (Health and Human Services) መምሪያ ወይም ከትምህርት ቤት ሠራተኛ(ኞች) ሊገኝ ይችላል። ቅጹ እና የሚጠየቁት ክትባቶች ልጁ/ልጅቷ ትምህርት ቤት ከመጀመሩ/ከመጀመሯ በፊት መሞላት አለባቸው። (ቅጽ MDH 896)
- ለጤንነት የሚያሰጉ አካባቢዎች ተብለው በተከለሉ አካባቢዎች የሚኖሩ ተማሪዎች ወይም ቀዳሚ አፀደ ህፃናት፣ ሙዓለ ህፃናት፣ እና 1ኛ ክፍል በመጀመሪያ በ Medicaid የገቡ፣ እና ጃንዋሪ 1/2015 ወይም ከዚያ በኋላ የተወለዱ ልጆች <u>በሙሉ</u> lead የተባለ የደም ምርመራ ውጤት/ማስረጃ ያስፈልጋቸዋል። የሜሪላንድ የጤና መምሪያ እና የአእምሮ ሃይጂን የደም Lead ምርመራ ሠርተፊኬት (DHMH 4620) ወይም በተፈቀደለት የጤና አገልግሎት ሰጪ ባለሙያ የተፈረመበት ማስረጃ ይህንን መስፈርት ለማሟላት መጠቀም ይቻላል።

ከተማሪዎች ቤተሰብ ኃይማኖት፣ እምነት፣ እና ልማድ ጋር የሚቃረን ከሆነ ክትባት ሊታለፍ ይችላል እና MDH ቅጽ 896 ላይ ወላጅ/ሞግዚት መፈረም አለባቸው። የተፈቀደለት የጤና ባለሙያ በሠርተፊኬት ካረጋገጠ በጤንነት ምክንያት ክትባት እንዳይሰጥ የተማሪዎች ክትባት ሊታለፍላቸው ይችላል። ከቤተሰብ ኃይማኖት እምነት እና ልማድ ጋር የሚቃረን ከሆነ የደም lead ምርመራው ሊታለፍ ይችላል። የመጠየቂያ ወረቀቱ መሠራቱን በማረጋገጥ የደም Lead ምርመራ ሠርተፊኬቱ በተፈቀደለት የጤና ባለሞያ መፈረም አለበት።

በዚህ ቅጽ ላይ የሚገኘውን የጤና መረጃ መስጠት የሚቻለው በልጅዎ ጤንነት ሁኔታ ላይ በህጋዊነት የሚመለከታቸው የጤና እና የትምህርት ሠራተኞች ለሆኑት ብቻ ነው።

ልጅዎ ከእነርሱ ትምህርታዊ ልምድ የበለጠውን ማግኘት እንዲችል/እንድትችል ለማገዝ፣ እባክዎን የዚህን የአካል ምርመራ ቅጽ ክፍል 1 ይሙሉ። ክፍል 2 በተፈቀደለት የጤና እንክብካቤ አቅራቢ መሞላት አለበት፣ ወይም የልጅዎን የአካል ምርመራ ከዚህ ፎርም ጋር አያይዙ። ልጅዎ መድሃኒት ካስፈለገው/ጋት ወይም ት/ቤት ውስጥ ህክምና መደረግ ካለበት፣ ለእያንዳንዱ መድሃኒት ወይም መከናወን ያለበት ህክምና የተፈቀደለት የጤና ባለሙያ የመድሃኒት ወይም መከናወን ስላለበት ህክምና የሞላው ፎርም እንዲኖራችሁ ያስፈልጋል። እነዚህን ቅጾች ከልጅዎ ት/ቤት፣ ወይም ከሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ድረ-ገጽ ላይ ለማግኘት ይቻላል www.montgomeryschoolsmd.org MCPS ቅጽ 525-12, በህክምና የታዘዘ መድኃኒት ለመስጠት ፈቃድ መስጫ, Release and Indemnification Agreement, MCPS ቅጽ 525-13, በህክምና የታዘዘ መድኃኒት ለመስጠት ፈቃድ መስጫ ስምምነት, Release and Indemnification Agreement, MCPS ቅጽ 525-14, Anaphylaxis ለሚያመው/ለሚያማት ተማሪ አስቸኳይ እርዳታ ለማድረግ ፈቃድ መስጫ ስምምነት, Release and Indemnification Agreement for Epinephrine Auto Injector. የተፈቀደለት የጤና እንክብካቤ ከሌላችሁ ወይም ልጃችሁ ልዩ ግላዊ የጤና እንክብካቤ ካስፈለገው/ካስፈለጋት፣ እባካችሁ ከልጃችሁ ት/ቤት ርእሰመምህር ወይም ነርስ ጋር ተገናኙ።

**እባክዎን ይህንን የአካል ምርመራ ቅጽ ይሙሉ እና ለልጅዎ ትምህርት ቤት በተቻለ ፍጥነት ይመልሱ።**

| ክፍል 1 የጤና ግምገማ<br>በወላጅ/አሳዳጊ የሚሞላ | | | የ MCPS የመታወቂያ # |
|---|---|---|---|
| የተማሪው/ዋ ስም (አያት፣ መጠሪያ፣ አባት)<br>(ለመጠራት የሚመርጠው/የምትመርጠው ስም) | የትውልድ ቀን<br>(ወር፣ ቀን፣ ዓ.ም) | የትምህርት ቤት ስም | ክፍል |
| አድራሻ (መንገድ፣ ከተማ፣ ስቴት፣ ዚፕ ኮድ) | | | ስልክ ቁ. |
| የወላጅ/አሳዳጊ ስም | | | |
| ለመደበኛ የህክምና እንክብካቤ ልጅዎን ብዙውን ጊዜ የት ይወስዳሉ?<br>ስም፡- | አድራሻ፡- | | ስልክ ቁ. |
| ልጅዎ መቼ ነው ለመጨረሻ ጊዜ የአካል ምርመራ ያደረገው/ያደረገችዉ? ወር | አመት | | |
| ልጅዎ መቼ ነው ለመጨረሻ ጊዜ የጥርስ ምርመራ ያደረገው/ያደረገችው? ወር | አመት | | |
| ለጥርስ እንክብካቤ አብዛኛውን ጊዜ ልጅዎን የት ይወስዳሉ?<br>ስም፡- | አድራሻ፡- | | ስልክ ቁ. |

**የተማሪ የጤና ግምገማ**

እርስዎ እስከሚያውቁት ድረስ፣ ልጅዎ ከዚህ ከሚከተሉት ማንኛውም አለበት/አለባት ወይ? እባክዎ አዎን ወይም አይደለም በሚለው ከዚህ በታች ምልክት አድርጉበት።

| | አዎን | አይደለም | አስተያየቶች |
|---|---|---|---|
| Anaphylaxis/አናፊላክሲስ ወይም ሃይለኛ የአለርጂክ ማገርሸት | | | |
| አለርጂዎች (ምግብ፣ ነፍሳት፣ መድሃኒቶች፣ ላቴክስ) | | | |
| አለርጅዎች (ወቅታዊ) | | | |
| አስም ወይም የመተንፈስ ችግሮች | | | |
